
# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 052 ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# የዓባይ ግድብ ለተፋሰሱ ሀገራት የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ገጸ በረከት ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨት ባሻገር ለኢትዮጵያም ሆነ ለተፋሰሱ ሀገራት የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ገጸ በረከት ነው ሲሉ በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት የጄነቲክ ሀብት አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ምርምር መሪ ሥራ አስፈፃሚ አብዮት ብርሃኑ (ዶ/ር) ተናገሩ።

አብዮት ብርሃኑ (ዶ/ር) ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት ዓለምን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተኑ ካሉ ችግሮች መካከል የአየር ንብረት ለውጥ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። የዓባይ ግድብ ከሌሎች ትሩፋቶቹ ባለፈ ለተፋሰሱ ሀገራት የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ገጸ በረከት ነው።

ግድቡ የኢትዮጵያንም ሆነ የአካባቢውን የአየር ንብረት ሚዛን በማስጠበቅ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ያሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ የግድቡ በውሃ መሞላት በአካበቢው የሚኖረውን የሙቀት መጠን መጨመር እና የሚከሰተውን ጎርፍ በመከላከል የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ገጸ በረከት መሆኑን ገልጸዋል።

እንዲሁም ግድቡ ለተፋሰሱ ሀገራት ዓመቱን ሙሉ ንጹህ ውሃ

የዓባይ ግድብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የአሰባሳቢ ትርክት አንድምታና ግቦች

**ሄለን ወንድምነው**

ከዚህ ቀደም ሲነገሩ የቆዩ የሀሰት ትርክቶች በኢትዮጵያ ላይ የግጭትና የመበተን አደጋ ጋርጠውባት የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን አሰባሳቢ ትርክቶችን የመገንባት እሳቤ እየጎላ መጥቷል። የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘወዴ በዓመቱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመክፈቻ ንግግራቸው ከአስቀመጧቸው የትኩረት አቅጣጫዎች መካከል አንዱ አሰባሳቢ ትርክቶችን በመፍጠር ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ትኩረት ማድረግ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት በነበሩት ጊዜያት በታኝ ትርክቶች በመስፋፋታቸው ምክንያት የእኔ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ ፣ ብሄር፣ ጎሳ፣ ኃይማኖት፣ ማንነትና እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚሉ እሳቤዎች በተለያዩ ቦታዎች ግጭት ሲቀሰቀስ፣ በዚህ ምክንያትም በሀገርና በዜጎች ላይ ጉዳት ሲደርስ ቆይቷል።

ትርክት ለሰው ልጆች የሚነገሩ የመረጃዎች፣ የእውነታዎች፣ የታሪኮች፣ የአፈ ታሪኮች እና የክስተቶች ድምር ውጤት እንዲሁም የእውቀት እና የስሜት አቅምን የሚገነባ የመረጃዎች ፍሰት ኃይል መሆኑን

የአሰባሳቢ ትርክት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በበጋ መስኖ ስንዴ 334 ሺ 937 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- እስካሁን ድረስ በበጋ መስኖ ስንዴን ለማልማት በተሠራው የእርሻ ሥራ 334 ሺህ 937 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

የግብርና ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል። በአሁኑ ወቅትም ወደ ተጨባጭ ተግባራት በመሸጋገር 334 ሺህ 937 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል።

በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በአፋር ክልሎች ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ እርሻ ሥራዎች ተከናውነዋል ያሉት አቶ ከበደ፤ በእነዚህ ክልሎች የተከናወነው የቅድመ እርሻ ሥራም እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ.ም በነበረው ጊዜ ውስጥ መጠናቀቁን ነው የገለጹት።

በክልሎቹ የተከናወነው የቅድመ እርሻ ሥራ በዘመናዊና በባህላዊ መንገድ መከናወኑን የገለጹት አቶ ከበደ፤ 738 ሺህ 430

በበጋ መስኖ ስንዴ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል














ሲዲያ ግርማ

# ከ465 ሺህ 726 በላይ የሠላም ሠራዊት ከጸጥታ መዋቅሩ ጋር እየሠሩ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የመዲናዋን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ከህብረተሰቡ የተውጣጡ 465 ሺህ 726 የሰላም ሠራዊት አባላት ከፀጥታ መዋቅሩ ጋር በጋራ እየሠሩ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ

ከ465 ሺህ 726... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# በክልሉ 85 ሺህ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት እየጠበቁ ነው

## - ለ61 ሺህ ዜጎች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ሕክምናው እየተሰጠ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- 85ሺህ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎትን በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙ የኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት ለ61 ሺህ ዜጎች አገልግሎቱን ለመስጠት እየተሠራ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በቢሮው ትኩረት የሚሹ የሀሩራማ በሽታዎች ባለሙያ አቶ አየለ ማሞ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የትራኮማ በሽታን ለመከላከል ከሚደረጉ ሕክምናዎች መካከል ዋነኛው የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም በኦሮሚያ ክልል 85ሺህ ዜጎች አገልግሎቱን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።

ከዓይን ቆብ መቀልበስ ጋር ተያይዞ ለዓይነ ስውርነት የሚያጋልጠውን የትራኮማ በሽታን የመከላከልና የማከም ሥራ በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ሆስፒታሎች እየተሰጠ ይገኛል ብለዋል።

በ2016 በጀት ዓመት ለ61 ሺህ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና አገልግሎትን ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ በክልሉ በሽታውን ለመከላከል ብዛት ያላቸው ወረዳዎች ላይ የመድኃኒት አቅርቦትና ሕክምና እንደሚያስፈልጋቸው አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት በክልሉ 243 ወረዳዎች ላይ የሚገኙ ዜጎች በበሽታው ተጠቂ መሆናቸውን ያነሱት አቶ አየለ፤ በክልሉ 28 ሚሊዮን ዜጎች ለበሽታው ተጋላጭ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

እንደ አቶ አየለ ገለጻ፤ ትራኮማን ቀድሞ ከመከላከል አንጻር የራስንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ ዋነኛው ተግባር ነው። በክልሉ ከሚገኙ ሰባት ሺህ ቀበሌዎች ውስጥ 56 በመቶ የሚሆነው ነዋሪ ከመጸዳጃ ቤት ውጭ



እንዳይጸዳዳና ንጽህናውን እንዲጠብቅ ማድረግ ተችሏል፡፡

የበሽታውን ስርጭት ለመግታት በየትምህርት ቤቶች ክበባትን በማቋቋም የፊት መታጠብና የግል ንጽህና አጠባበቅ ላይ ሰፊ ትምህርቶች በመስጠት ላይ ናቸው ያሉት አቶ አየለ፤ ህብረተሰቡ በተለያዩ ፕሮጀክቶች የንጹህ ውሃ አገልግሎት እንዲያገኝ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪ በተለያዩ ወቅቶች በሽታውን ለማከም የሚረዳ የመድኃኒት አቅርቦት ስርጭት ከ35 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ዜጎች መዳረሱን አመልክተዋል።

በክልሉ ከፍተኛ የበሽታው ስርጭት ምጣኔ ያለው ምስራቅ ሀረርጌ አካባቢ መሆኑን ጠቁመው፤ በተጨማሪም በምዕራብ ሀረርጌ፣ በጅማ፣ በአርሲ አካባቢ፣ በሆሮጉድሩ ወለጋና ማዕከላዊ ኦሮሚያ ላይ በስፋት እንደሚታይ ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ ከ እ.አ.አ 2014 ጀምሮ የተጠናከረ የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና አገልግሎት በማቅረብ 233 ሺህ ዜጎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

በሽታውን ለመከላከልም የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና አገልግሎትን ከመስጠት በተጨማሪ የመድኃኒት እደላ ማከናወን የንፁሁ ውሃ አቅርቦት፣ የግል ንጽህና አጠባበቅ ዙሪያ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች በስፋት እንደሚከናወኑ አቶ አየለ ገልጸዋል፡፡

# በከተማዋ በቴክሎጂ የታገዘ የተቀላጠፈ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ተሰጥቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ በሩብ ዓመቱ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት መስጠት መቻሉን የአዲስ አበባ ሥራ አስኪያጅች ጽህፈት ቤት ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት የተጠሪ ተቋማት የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የሩብ ዓመት አፈጻጸምን ገምግሟል፡፡

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስኪያጅ ጥራቱ በየነ እንደገለጹት ፤ በከተማ አስተዳደሩ በሩብ ዓመቱ ለመፈጸም በዕቅድ ከያዛቸው ተግባራት በቴክኖሎጂ የታገዘ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት በመስጠቱ የተነሳ ከከተማ እስከ ወረዳ ያለው መዋቅር ጥሩ የሚባል አፈጻጸም አስመዝግቧል፡፡

ባለፈው ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በከተማና በክፍለ ከተማ የሚታቀዱ እቅዶች ያለመናበብ ክፍተት ይስተዋል እንደነበር አውስተው፤ ዘንድሮ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ይህ ክፍተት መስተካከሉን ተናግረዋል፡፡

አቶ ጥራቱ በሩብ ዓመት አፈጻጸሙ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ መደገፍ በመቻሉ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት መስጠት መቻሉን ገልጸው፤ በቀጣይም ሁሉንም ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ በማድረግ የበለጠ መስተንግዶውን ማሻሻል እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

አገልግሎቶቹ ከባለፉት ጊዜያት ሲነጻጸሩ የተሻለ ይሁኑ እንጂ አሁንም ዓለም አቀፋዊ ደረጃን ያላሟሉና ሙሉ በሙሉ የሚነሱ የሕዝብ ቅሬታዎችን ያልፈቱ ናቸው ብለዋል፡፡



የአገልግሎቶቹ ክፍተት ከቴክኖሎጂና ከአሠራር ጋር የሚያያዝ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህን ክፍተት ለመፍታት ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠትና አሠራራቸውን በቴክኖሎጂ በመደገፍ አገልግሎቱን ማዘመን እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የተቻለበት ሌላኛው ምክንያት ተቋማት በቅንጅት መሥራት በመቻላቸው መሆኑን ገልጸው፡ ለዚህም ማሳያው በመዲናዋ የተከበሩት ሕዝባዊና ኃይማኖታዊ በዓላት ወቅት የተሟላ የኤሌክትሪክና የውሃ አገልግሎት መሰጠቱን በአብነት ጠቅሰዋል፡፡

የጽዳት ኤጀንሲ ፣ውሃና ፍሳሽ ፣ እሳት አደጋና ኤሌክትሪክ አገልግሎት በቅንጅት ከሠሩ ተቋማት መካከል መሆናቸውን ተናግረው፤ የታየውን ተነሳሽነት ከበዓላት ባለፈ ሁሌም ማስቀጠል እንደሚገባ መክረዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ በሩብ ዓመቱ በከተማዋ ጥሩ የሚባል አፈጻጸም ቢኖርም በከተማዋ የጽዳት ደረጃዎች ላይ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማሳደግ፣ በማእከል ደረጃ የጋራ ሪፎርም ማድረግ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በሙሉ አቅም ለመሥራት ምክክር ማድረግ ታቅደው ያልተከናወኑ ሥራዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

# ክልሎች ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚያመች ወጥ አደረጃጀት ፈጠሩ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ -ክልሎች ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚያመች ወጥ አደረጃጀት መፍጠራቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ሚኒስቴሩ ይህንን የገለጸው የ2016 ዓ.ም የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ትናንት በገመገመበት ወቅት ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ታረቀኝ ቡሉልታ እንደገለጹት፤ ከዚህ በፊት እንደ ችግር ሲነሱ የነበሩ የክልሎች አደረጃጀት ወጥ ያለመሆን ችግር አምራች ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ አስቸጋሪ አድርጎት ቆይቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ተስተካክሎ ክልሎች ወጥ አደረጃጀቶች መፍጠር ችለዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸው የምርት ግብዓት፣ ፋይናንስ ፣የኤሌክትሪክ ኃይል እና የሠለጠነ የሰው ኃይል መለየቱን ገልጸው፤ ክልሎች ለአምራች ኢንዱስትሪው ድጋፍ የሚያመች ወጥ አደረጃጀት መፍጠራቸው ለዘርፉ ዕድገት ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን ተቋማዊ ለማድረግ ከክልሎች ጋር ከስምምነት ተደርሶ ክልሎች በጀት መያዛቸውን አውስተው፤ ይህ መልካም ጅማሮ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የብድር አቅርቦት ላይ የሥራ ማስኬጃ ብድር አቅርቦት እና የሊዝ ፋይናንሲንግ ብድር አቅርቦት አሁንም በልዩ ትኩረት መከታተል እንደሚያስፈልግ መገምገማቸውንም ጠቁመዋል፡፡

የአነስተኛ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን የመረጃ አያያዝና ተከታትሎ የመደገፍ የማደራጀት ሥራ በሩብ ዓመቱ እንደ ውስንነት መታየቱንም አመልክተዋል፡፡

አብዛኛው የሥራ ዕድል የሚፈጠርበት የአነስተኛና የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች መሆናቸውን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከምስረታና ከሽግግር ጋር ያሉ ሥራዎችን መደገፍ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

የጸጥታ ችግር አጋጥሚቸው በነበሩባቸው አካባቢዎች በተለይ በአማራ ክልል አካባቢዎች ሕብረተሰቡ አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ጉዳት እንዳይደርስበት ያደረገው ጥረት እጅግ አበረታች መሆኑን አውስተው፤ ኢንዱስትሪዎች ግጭቶች ቢኖሩም በሕብረተሰቡ ትብብር ጉዳት እንዳላጋጠማቸው ተናግረዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎቹ ያመረቱትን ምርት ለገበያ ለማቅረብና የምርት ግብዓት ለማግኘት ችግር ማጋጠሙን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የጸጥታ ሁኔታው ሲሻሻል የተመረተውን ምርት ወደ ገበያና የግብዓት አቅርቦት ችግሮችም እንደሚፈቱ ጠቁመዋል፡፡

ሁሉንም ክልሎች በአካል በመገኘት የምልከታ ሥራ መከናወኑንም ገልጸው፤ ምልከታው ከክልሎች ጋር በሩብ ዓመቱ በዕቅድ ዝግጅት መስማማት ላይ የተደረሰባቸውን የታቀዱ ሥራዎች መከናወናቸውን ለመገምገም መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የመጀመሪያው ሩብ ዓመት አብዛኛው የዝግጅት ወቅት መሆኑን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ በምልከታው እንደታየው በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የተሻሉ መነቃቃቶች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

በመድረኩ ክልሎች የሩብ ዓመት አፈጻጸማቸውንና በሩብ ዓመቱ ያጋጠማቸውን ችግሮች አቅርበዋል፡፡ በሩብ ዓመት አፈጻጸሙ የክልል የቢሮ ኃላፊዎች ፣ የከተማ መስተዳደሮች እንዲሁም የሚኒስቴሩ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተገኝተዋል፡፡

# የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ከኢንዱስትሪ ምርቶች ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር አገኘ


**ሞገስ ጸጋዬ**

ድሬዳዋ፡- የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በወጪ ንግድና በተተኪ ምርት ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ማስገኘቱን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አክሊሉ ታደሰ እንደገለጹት፣ መንግሥት ሀገራችንን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግ የተለያዩ የፖሊሲ የማሻሻያዎችን አድርጓል፡፡ በዚህ ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ባለሀብቶች የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ገብተው እያመረቱ ይገኛሉ፡፡ በዚህም በወጪ ንግድና በተተኪ ምርት ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ተገኝቷል፡፡

ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት ምቹ የማድረግ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመው፤ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚገመት ገቢ ከወጪ ንግድና ተተኪ ምርት ማስገኘት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ነጻ የንግድ ቀጣናው በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ከፍተኛ ገቢ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚን ይደግፋል ያሉት




አቶ አክሊሉ፤ በአሁኑ ጊዜ ከሁለት ሺህ ሶስት መቶ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

የድሬዳዋ ነጻ ንግድ ቀጣና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለደንበኞቹ መስጠት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን ማሟላቱን ሥራ አስፈጻሚው አመልክተው፣ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል፣ የባለሀብት መመልመያ መስፈርትና የአገልግሎት ዋጋ ተመን መዘጋጀቱን ጠቅሰዋል።

በአሁኑ ጊዜም ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ያስመዘገቡ ባለሀብቶች ከኮርፖሬሽኑ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመው ሥራ ለመጀመር የሚያስችላቸውን የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ መጽደቅ በመጠባበቅ ላይ ናቸው ብለዋል።

አዋጁ በቅርቡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመራ በመሆኑ ባለሀብቶች በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገቡ አስታውቀዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውጤታማ እንዲሆን የተለያዩ ሀገራት በነጻ ንግድ ቀጣና አስተዳደር ዙሪያ ያላቸው ተሞክሮና ልምድ ተወስዷል፡፡ የተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች፣ የቱርክና የጂቡቲ ተሞክሮ በስፋትና በጥልቀት ተዳሷል። እንዲሁም ነጻ የንግድ ቀጣናው ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆን የሚያስችሉ አሠራሮች ተቀርጸው እየተተገበሩ ይገኛሉ።

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ መግባት የዋጋ ግሽበትን በመቀነስ፣ የግብርና ግብዓቶችን አቅርቦት በማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት ፍላጎትንና የንግድና የሎጅስቲክስ አገልግሎቶችን በማሻሻል ረገድ ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ነጻ የንግድ ቀጣናው በ150 ሄክታር ላይ ያረፈው ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፣ ነጻ ንግድ ቀጣናው የመሠረተ ልማት አቅርቦት ማለትም የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የቴሌኮም አገልግሎት፣ የውሃ አቅርቦት ፣ የፍሳሽ ማጣሪያ የተሟሉለት ሲሆን ለቢሮና ለንግድ የሚሆኑ ህንፃዎች በውስጡ ይዟል።

እንዲሁም ለማምረቻና ለመጋዘንነት የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች ሲኖሩ በቀጣይ የሚለማ 4000 ሄክታር የማስፋፊያ ቦታንም ማካተቱ ታውቋል።

# ማዕከሉ በ300 በሽታዎች ላይ ጥናቶችን እያካሄደ ነው

**አመስወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ከ300 በላይ በሽታዎች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን እያከናወነ እንደሚገኝ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የብሔራዊ ጤና ማደራጃና ትንተና ማዕከል አስታወቀ።

የበሽታዎችን ተጽዕኖ ለመለየትና ያለመ አውደ ጥናት በተካሄደበት ወቅት የማዕከሉ አማካሪ አወቀ ምስጋናው (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ማዕከሉ በሀገሪቱ የሚገኙ 300 በሽታዎች ላይ ዝርዝር ጥናት እያካሄደ ይገኛል።

ጥናት ከሚደረግባቸው በሽታዎች መካከል ከ50 እስከ 60 በሚደርሱ በሽታዎች ላይ ልዩ ትኩረት ተደርጎ እንደሚሠራም አመላክተዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች ካንሰር፣ የደም ግፊት፣ ስኳር፤ ከመተንፈሻ አካላት ጋር ተያይዘው የሚመጡ በሽታዎችና የልብ ሕመም ሰፊ የጤና ተጽዕኖ በማድረስ ረገድ ዋነኞቹ ሲሆኑ በዘርፉ ችግር ፈቺ



ጥናቶች እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

ለበሽታዎቹ አጋላጭ መንስኤዎችን የማጥናትና ከእያንዳንዱ ክልል የኑሮ ዘይቤ ጋር ተያይዞ ያለውን ተጋላጭነት እንዲሁም በሽታው በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በሌሎች ዘርፎች ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖ ለመለየት የሚያስችል ጥናት እንደሚካሄድ አስረድተዋል።

በተጨማሪ በሀገሪቱ የተሻለ የማህበረሰብ ጤና ሥርዓት እንዲኖር የጤናው ዘርፍ ከሌሎች ዘርፎች ጋር በጋራ እንዲሠራበት፣ በቂ በጀት እንዲመበድና የትኛው ክልል በየትኛው በሽታ የበለጠ እንደሚጠቃ ለመለየት ማዕከሉ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ አመላክተዋል።

በጤናው ዘርፍ በሚያካሂዳቸው ጥናት መሠረት በሀገሪቱ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚበጀተው በጀት 25 በመቶ እንዲጨመር ተደርጓል፡፡

ማዕከሉ ጥናቶችን የሚያከናውነው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከክልልና ከፌዴራል የጤናና የምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት መሆኑን ገልጸዋል።

በጤናው ዘርፍ በሚከናወኑ ጥናቶች መሠረት ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚበጀተው በጀት እንዲያድግ ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

አማካሪው እንደተናገሩት፤ ማዕከሉ በሀገር አቀፍ ደረጃና በክልል በሚያከናውናቸው የበሽታ ተጽዕኖ ጥናቶች አማካኝነት ለፖሊሲ ዝግጅትና ለተለያዩ ሥራዎች የሚሆን ግብዓት ለመንግሥትና ለተለያዩ ተቋማት እያቀረበ ይገኛል።

ዶክተር አወቀ እንደገለጹት፤ ማዕከሉ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራውን ጥናት አጠናክሮ ይቀጥላል።

# የደቡብ ኮሪያዋ ቹን ቾንና አዲስ አበባ ግንኙነታቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታወቁ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባና የደቡብ ኮሪያዋ ቹን ቾን ከተማ ለ60 ዓመታት የዘለቀውን የወዳጅነትና የትብብር ግንኙነታቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ አስታወቁ።

አዲስ አበባና የደቡብ ኮሪያዋ ቹን ቾን ከተማ 60 ዓመት የዘለቀ ግንኙነት ቢኖራቸውም በይፋ የእህትማማችነት ግንኙነት የጀመሩበት 20ኛ ዓመት ሰሞኑን ተከብሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አበቤ የ20 ዓመታት በዓሉን ለማክበር የመጡትን የቹን ቾን ከተማ ከንቲባ ዩክ ዶንግ ሀንና ልዑካቸውን በተቀበሉበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ሁለቱ ከተሞች የዛሬ 60 ዓመት ጀምሮ በደም የተሳሰረ ግንኙነት አላቸው።

ከተማዋ የዛሬ 60 ዓመት ለደቡብ ኮሪያ ነጻነት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን መስዋእትነት የከፈሉባት ናት ያሉት ከንቲባዋ፤ ባለፉት ዓመታትም ሁለቱ ሀገራት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በርካታ ሥራዎችን በትብብር ሲሠሩ ቆይተዋል ብለዋል።

ባለፈው ነሐሴ ወር ወደ ኮሪያው ቹን ቾን በማቅና የሁለቱን ከተሞች ግንኙነት ለማጠናከርና በትብብር ለመሥራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ውይይቶችን አከናውነናል ሲሊ ከንቲባዋ ገልጸዋል።

በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ላመጡ የአዲስ አበባ ተማሪዎችና ሠራተኞች የትምህርት ዕድል በመስጠት ቹን ቾን ከተማ ድጋፍ ማድረጓን ጠቁመው፤



በቴክኖሎጂ፣ በባህል ልውውጥና በሌሎች ዘርፎችም ትብብርን በማጠናከር የተከናወኑ ሥራዎች የሚበረታቱ መሆናቸውን ተናግረዋል።

የኮሪያ የከተሞች ዕድገት ሞዴል ለኢትዮጵያም አርዓያ የሚሆን ሥራ በመሆኑ ልንማርበትና ከእኛ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ልናዋህደው ይገባናል ሲሉ አስረድተዋል።

የቹን ቾን ከተማ ከንቲባ ዮክ ቶንግ ሃንና ልዑካን ቡድናቸውን ተቀብለን ስናስተናግድ ለላቀ ሥራ ራሳችንን በማዘጋጀት ጭምር ነው ብለዋል።

አዲስ አበባ ከተማ ካሏት 24 እህት ከተሞች አንዷ የሆነችው ከቹን ቾን ከተማ ከንቲባና ልዑካኑ ጋር ያደረግነው ውይይት ፍሬያማ ነው ሲሉ አመላክተዋል።

የደቡብ ኮሪያ ቹን ቾን ከተማ ከንቲባ ዩክ ዶንግ ሀን በበኩላቸው፤ የዛሬይቷን ደቡብ ኮሪያ እንድናይ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የከፈሉት መስዋእትነት ትልቅ ድርሻ አለው፤ ይህ ተጋድሎ ዛሬ ሁለቱ ሀገራት ለደረሱበት መልካም ግንኙነት መሠረት የጣለ ነው ብለዋል።

በተለይም የቹን ቾን ከተማን ነጻ ለማውጣት በተደረገው ተጋድሎ ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውን በማስታወስ ይህንን የሚዘክር ሐውልት በከተማዋ መቆሙንና ሙዚየም መገንባቱን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በየወቅቱ ለውጥ እያስመዘገበች ትገኛለች ያሉት ከንቲባው፤ በቀጣይም ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትን ይዛ እንደምታድግ ሙሉ እምነት አለኝ ሲሉ ተናግረዋል።

በተያያዘም ደቡብ ኮርያዋ ቾን ቹን ከተማ ሁለት ሺህ መጻሕፍትን ትናንት ለአዲስ አበባ ከተማ አብርሆት ቤተ መጻሕፍት አበርክታለች።

መጻሕፍቱን የቾን ቹን ከተማ ከንቲባ ዮክ ዶንግ ሀን ለአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ አስረክበዋል።

የእህትማማችነት ግንኙነቱን የሚያጠናክሩ ሌሎች ተጨማሪ የትብብር መስኮችን ለማስፋት እንደሚስሩ የገለፁት ከንቲባ ዮክ ቶንግ ሃን በአብርሆት ቤተ መጻሕፍት በተዘጋጀው ኮርነር ሁለት ሺህ መጻሕፍት አበርክተዋል፡፡

20ኛ ዓመት የእህት ከተማነት ግንኙነታቸውን እያከበሩ የሚገኙት ሁለቱ ከተሞች ግንኙነታቸውን በባህል ልውውጥ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በትምህርት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር መስኮች ለማጠናከር እየሠሩ እንደሚገኙ ተገልጿል።

የኮደቡብ ኮሪያና የኢትዮጵያም ሆነ የአዲስ አበባና የቹን ቾን ከተማ የትብብርና የወዳጅነት ግንኙነትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፤ ግንኙነቱም በሚቀጥሉት ትውልዶች ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚጠበቅብንን ሁሉ ለመሥራት ዝግጁ ነን ሲሉ ከንቲባዎቹ ቃል ገብተዋል።

ዜና

# በመዲናዋ የመኪና መብራት አጠቃቀም ላይ ልዩ ክትትል ሊደረግ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ረጅም የመኪና መብራት አጠቃቀም ላይ ልዩ ክትትል እንደሚደረግ የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ማስከበርና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ አያሌው አቲሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በከተማ ውስጥ ረጅም የመኪና ማብራት ፈጽሞ አይፈቀድም። ህጉም በግልጽ ይህን ይከለክላል። ነገር ግን አሁን ላይ በመዲናዋ ረጅም የመኪና መብራት የሚጠቀሙ አካላት እየተስተዋሉ ይገኛል።

ይህን የሕግ መተላለፍ ለመግታት በመዲናዋ ረጅም የመኪና መብራት አጠቃቀም ላይ ልዩ ክትትል ይደረጋል ያሉት አቶ አያሌው፤ በቁጥጥር ሂደቱ ውስጥ ሕግ ተላልፈው የተገኙ አካላት ተቆጣጣሪዎች ሕጉን መሠረት ያደረገና ከመደበኛው ቅጣት ከፍ ያለ ርምጃ እንዲወስዱ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ሕግ መተላለፍ በሰው ላይ ከሚያስከትለው የሞት እና የአካል ጉዳት ባሻገር በግለሰብና በመንግሥት ሀብት ላይ የሚያስከትለው ኪሳራ ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ አያሌው፤ በከተማ ውስጥ ረጅም የመኪና መብራት መጠቀም አሽከርካሪዎች በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ ይዳርጋል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ በተሽከርካሪው ላይ ያልነበረ ሌላ ተጨማሪ የመብራት አካል እየገጠሙ የሚጠቀሙ አሽከርካሪዎች አሉ። ተግባሩ በቀጥታ ደንብ የተላለፈ በመሆኑ ቅጣቱ ከመደበኛ ቅጣቶች ከፍ ያለ እንዲሆን ተደርጓል። አሽከርካሪዎች ይህ ድርጊት በሰውና በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ ከዚህ ተግባራቸው ሊቆጠቡ ይገባል።

አሁን ላይ የሌላ ተሽከርካሪ የፊት መብራት አስገጥመው የሚጠቀሙ በርካታ አሽከርካሪዎች ርምጃ እየተወሰደ ነው ያሉት አቶ አያሌው፤ በመዲናዋ የመኪና መብራት አጠቃቀም ላይ ልዩ ክትትል ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ልዩ ክትትሉ ራሱን የቻለ እቅድ፣ የአፈፃጸም ሥርዓት፣ የቅጣት ደረጃ፣ የሰው ኃይል እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በውስጡ ተካተዋል ያሉት አቶ አያሌው፤ ደንብ ጥሰቱ ከሌሎች ጥሰቶች እኩል የሚታይ አለመሆኑን አሽከርካሪዎች ሊገነዘቡ ይገባል ብለዋል።



አቶ አያሌው አቲሳ

# የአሰባሳቢ ትርክት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

አሰባሳቢ ትርክት ምንድን ነው፣ አሰባሳቢ ትርክትን መፍጠር የማን ኃላፊነት ነው፣ የመንግሥት፣ የምሁራንና የእያንዳንዱ ግለሰብ ሚና ምንድን ነው፣ የአሰባሳቢ ትርክት መዳረሻ ምን ሊሆን ይችላል በሚሉት ሃሳቦች ዙሪያ የታሪክ ምሁራን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የታሪክ ምሁርና የሀገር ሽማግሌ የሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ተሰባስበን መኖራችን እና ፈጣሪ የሰጠንን የተፈጥሮ ሀብት በጋራ መጠቀማችን በራሱ አሰባሳቢ ትርክት ነው ይላሉ።

ሀገራዊ (አሰባሳቢ) ትርክትን መፍጠር መንግሥት፣ ምሁራን እና እያንዳንዱ ግለሰብ ከፍተኛ ሚና አላቸው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ አስተዳደራዊ ችግሮችን መፍታት፣ ለወጣቱ ፍትሃዊ የሆነ የሥራ ዕድል በመስጠት፣ ፍትህንና ሰላምን ማስፈን፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ ችግር ያለባቸው መመሪያዎችንና የአሠራር ሥርዓቶችን ማስተካከል ከመንግሥት የሚጠበቅ መሆኑን ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ፣ የአፍሪካ መዲና፣ የነጻነት ምልክት ቀንዲል፣ የዓባይ ወንዝ ባለቤት መሆኗ እና መሰል ጉዳዮች ለአሰባሰቢ ትርክት ግብዓት የሚሆኑ በመሆናቸው በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ተካተው ትውልዱ ከልጅነታቸው ጀምረው እንዲያውቁት በማድረግ ሀገራዊ ትርክትን መገንባት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ አገላለጽ፤ ሀገር አቀፍ የሆኑ ተግባራትን መሥራት ከተቻለ አሰባሳቢ ትርክትን መፍጠር እና አጉልቶ ማውጣት ይቻላል። በተለይ አሁን ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ ባሉት የሽግግር ፍትህ እና ሀገራዊ ምክክር የተያዘላቸውን ግብ እንዲያሳኩ በማድረግ የነበሩትን ቁርሾዎች አስወግዶ ሀገራዊ ትርክትንና የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር ይገባል።

የሚያራርቅ ትርክትን አስወግዶ ሀገራዊ ትርክትን ለመገንባት ታሪክን ማወቅ፣ የሚከፋፍሉ ሃሳቦችንና ሁኔታዎችን አለመቀበል፣ ከምሁራንና ከማህረሰቡ የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን ያስረዳሉ።

ብሄራዊ ትርክትን መገንባት ግቦች ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ማጠናከር፣ ቅቡልነት ያለው ዴሞክራሲ መገንባት፣ በሕዝቦች መካከል ዘላቂ ወንድማማችነትና እህትማማችነት መፍጠር፣ የዜጎችን ክብርና ደህንነት ማስጠበቅ፣ የሕግ የበላይነትና ፍትህን ማረጋገጥ፣ የሀገርን ልማት እና እድገት ማፋጠን መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል የነገሮችን ትስስርና አመጣጥ ማወቅ፣ ለሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች የጋራ መፍትሄ ማስቀመጥ ይቻላል የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አህመድ፤ ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሰባሳቢ ትርክትን በመገንባት ሂደት ውስጥ የድርሻቸውን በመወጣት ከሚመጡት በረከቶች ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያስረዳሉ።

ሌላኛው የሶስተኛ ዲግሪ የታሪክ ተማሪ መብራቱ ጌርጊሶ በበኩላቸው፤ ሰዎች ያለፈውን ታሪክና አሁን ያለውን ሁኔታ የሚገልጹበት መንገድ ትርክት ሲሆን፤ ሀገራዊ ትርክትን ለመፍጠር የመንግሥትና የምሁራን ሚና ከፍተኛ ነው ይላሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የትርክት መዛነፎች በርካታ ጉዳቶች እያስከተሉ በመሆኑ ምሁራን ሀገራዊ (አሰባሳቢ) ትርክትን በማህበረሰቡ እና በሀገሪቱ ለመገንባት የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

ችግሮች ላይ የጋራ መፍትሄ ማስቀመጥ የሚቻለው ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል በመሆኑ፤ ሁሉም ማህበረሰብ መነጋገር፣ መከባበር፣ መደማመጥ፣ መግባባት እና አንድ መሆን እንደሚኖርባቸው ይገልጻሉ።

የሚፈጠረውን ሀገራዊ ትርክት ማህበረሰቡ እንዴት ሊቀበለው እንደሚገባ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ትውልዱ ተገንዝቦ ተግባራዊ እንዲያደርገው ማድረግ ተገቢ ነው ይላሉ።

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ትርክትን ለመገንባት ትልቁ ፈተና የሥልጣን ሽኩቻ፣ የፖለቲካ አለመግባባት እና አንድ ክልል ጥያቄ ሲመለስ የሌላው ጥቅም የሚነካ ተደርጎ መወሰዱ ነው የሚሉት አቶ ታምራት፤ ተቀራርቦ በመነጋገር ያሉትን ችግሮች መፍታት ተገቢ ነው ባይ ናቸው።

የሚፈለገውን ሀገራዊ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚቻለው ሀገራዊ ትርክትን መገንባት ሲቻል መሆኑን አምኖ በመቀበልና መተግባር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

የኢትዮጵያን አንድነትን አጠናክሮ ለማስቀጠል አለመግባባቶችን በውይይት መፍታት፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን ማቀራረብ እና ለጸብ መንስኤ የሚሆኑ ሃሳቦችን በማስወገድ ዘላቂ ሰላምን የሚያጸኑ ሃሳቦች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ሀገራዊ (አሰባሳቢ) ትረክትን መገንባት ህብረ ብሄራዊ አንድነትን ለማጠናከር፣ ቅቡልነት ያለው ዴሞክራሲ ለመገንባት፣ በሕዝቦች መካከል ዘላቂ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ለመፍጠር፣ የዜጎችን ክብርና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ የሕግ የበላይነትና ፍትህን ለማረጋገጥ፣ የሀገርን ልማት እና እድገት ለማፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ መንግሥት፣ ምሁራን እና ሁሉም ማህበረሰብ የድርሻቸውን ሊወጡ እንደሚገባ የታሪክ ምሁራት ይመክራሉ።

# ከ465 ሺህ 726...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ከአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ጋር የ2016 ዓ.ም የአንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ትናንትና ገምግሟል።

በወቅቱ የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ሊዲያ ግርማ እንደተናገሩት፤ በመዲናዋ 465 ሺህ 726 የሰላም ሠራዊት አባላት በ 121 ወረዳዎች በመደራጀት ከጸጥታ መዋቅሩ ጋር በጋራ እየሠሩ ይገኛል።

የሰላም ሠራዊቱ በመዲናዋ የሚስተዋሉ የጸጥታ ስጋቶችን በመለየት ከፀጥታ ተቋማት ጋር እየሠሩ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ የሰላም ሠራዊት አባላቱ ከማህበረሰቡ የተውጣጡና በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ እንዲሁም ከሁሉም ፆታዎች የተውጣጡ ናቸው። አሳታፊ በሆነ መንገድ የተመረጡ የሰላም ሠራዊት አባላት ለመዲናዋ ሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ ይገኛል።

የጸጥታ መዋቅሩና ሕዝቡ በጋራ በሠሩት ሥራ በመዲናይቱ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች የመቀነስ አዝማሚያ አሳይተዋል ሲሉ አስረድተዋል።

የከተማውን ነዋሪ ለማሳተፍ ተብሎ የተቋቋመውን የሠላም ሠራዊት አደረጃጀት በማጠናከርና አመርቂ ውጤቶች ተገኝተዋል ብለዋል።

የሠላም ሠራዊት አባላቱ ከተማዋን ማዕከል አድርገው ጥፋት ለመፈፀም የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ሠላም ኃይሎችን ለመቆጣጠር በተደረገው ጥረት ጉልህ ሚና መጫወታቸውን አስረድተዋል።

በመዲናዋ የሠላም ሠራዊቱን ባሳተፈ መልኩ በተከናወኑ የፍተሻና ቁጥጥር ሥራዎች በሕገ ወጥ መንገድ የተከማቹ የተለያዩ ሀገራት የገንዘብ ኖቶች፣ የጦር መሣሪያዎችና ወንጀል ፈጻሚ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ማዋል መቻሉን አመልክተዋል።

በመዲናይቱ በሩብ ዓመቱ ትላልቅ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የአደባባይ በዓላትን ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ያለምንም የፀጥታ ችግር ማክበሩን ያነሱት ኃላፊዋ፤ ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ የደንብ ማስከበርና ጠንካራ የፀጥታ ሥራ በመከናወኑ የጥፋት ኃይሎችን አጀንዳ ማክሸፍ መቻሉን አስረድተዋል።

በሩብ ዓመቱ የተከናወኑ የሠላምና ደህንነት ሥራዎች ሰላምና መረጋጋትን በመፍጠር ረገድ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣታቸውን ኃላፊዋ ገልጸዋል።

የህብረተሰቡን ተሳተፎ ማጎልበት፣ የፀጥታ ስጋትን መከላከል፣ የወንጀል ድርጊቶችን መቀነስ፣ የፀጥታ ተቋማትን ቅንጅታዊ አሠራር ማጎልበትና ሌሎችም በሠላምና ፀጥታው ዘርፍ ከተሠሩ ሥራዎች መካከል እንደሆኑ ጠቅሰዋል።

# የዓባይ ግድብ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንዲደርሳቸው የሚያደርግ መሆኑን አንስተው፤ የታችኛዎቹ የተፋሰሱ ሀገራት በጎርፍና በደለል የሚከሰተውን የብዝሃ ሕይወት ውድመትና ያንን ተከትሎ ከሚመጣ የአየር ንብረት ለውጥ እንደሚታደጋቸውም ጠቁመዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ፤ ድርቅና የብዝሃ ሕይወት ሀብቶች በድንበር የማይወሰኑ ናቸው ያሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ የዓባይ ግድብ አካባቢ በአረጓዴ መሸፈኑ በአካባቢው ባሉ ሀገራት የሚገኙ የብዝሃ ሕይወት ሀብቶችን ለመጠበቅ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ተናግረዋል።

ግድቡ አካባቢ የሚሠሩ የተፈጥሮ ሀብትና ጥበቃ ሥራዎች በአጎራባች ሀገራት አካባቢዎች እየተስፋፋ ያለውን በርሃማነት ለመግታትም እንደሚረዳ አመልክተው፤ እርጥበቱ ቋሚ በሚሆንበት ጊዜ በቦታው በተለያየ መንገድ በርካታ እጽዋት ይበቅላሉ፤ የግድቡ መኖር ከብዝሃ ሕይወት ሀብቶች አንዱ የሆነውን የተለያዩ ዝርያ ያላቸው የዓሳ ሀብት ልማት እንዲካሄድ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ አብዮት (ዶ/ር) ገለጻ፤ የዓባይ ወንዝ በራሱ የሚታወቅባቸው የዓሳ ዝርያዎች አሉ። እነዚህ ዝርያዎች ሀይቅ ሲሆን በመጠንም በአይነትም የሚጨምሩ ይሆናል። እነዚህን የዓሳ ምርቶች ተከትሎ የሚመጡ በርካታ ሌሎች እዋፋትና የምድር እንስሳትም ይኖራሉ። እነዚህ በዓባይ ግድብ የሚከትሙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ በተለያየ መንገድ ወደጎረቤት ሀገራትም መሄዳቸው አይቀርም።

በግድቡ ኤሌክትሪክ ኃይል ከማመንጨትና የዓሳ ልማት ከማካሄድ ባሻገር ከመላው ዓለም በዋናነት ከጎረቤት ሀገራት ለሚሰባሰቡ አዕዋፋት ለመራቢያነትና ለጊዜያዊ መጠለያነት የሚያገለግልም ነው። በተለይም በሀይቁ ዳርቻ የሚፈጠረው እርጥበታማ መሬት ለነፍሳትና እነሱን ለሚመገቡ አዕዋፋትና በደረታቸው ለሚሳቡ እንስሳት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

ከአርባ ምንጭ ቀጥሎ ሁለተኛውን የአዞ ርባታ ለመገንባት የሚያስችልም እንደሚሆን ገልጸው፤ የብዝሃ ሕይወት ከመጠበቅና እንዲበራከቱ ከማድረጉ በተጨማሪ ለኢኮ ቱሪዝም እንቅስቃሴውም የሚያበረክተው የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸዋል።

# በበጋ መስኖ ስንዴ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሄክታር መሬት በባህላዊ መንገድ መታረሱንና 193 ሺህ 269 ሄክታር መሬት ደግሞ በዘመናዊ መንገድ ወይም በትራክተር መታረሱን ተናግረዋል። አጠቃላይ በምርት ዘመኑ ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ብቻ ከተሰራው የቅድመ እርሻ ሥራ 334 ሺ 937 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን መቻሉን አመላክተዋል።

የቅድመ እርሻ ሥራው በሌሎች ክልሎችም ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን የጠቀሱት አቶ ከበደ፤ በሀገር ደረጃ በበጀት ዓመቱ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለመሸፈን መታቀዱን አስታውሰዋል።

ይህም ሁሉንም ክልሎች ያማከለ እንደሆነ ነው። ቀሪ ክልሎችም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን ለማከናወን የሚያስችላቸውን የቅድመ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን አቶ ከበደ ገልጸዋል።

የውሃ አማራጮች እና ሰፋፊ መሬቶች እያሉ መሬት ጦም አይደር በሚል በተለይም የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ሰፊ የንቅናቄ ሥራዎች መሠራታቸውን የጠቀሱት አቶ ከበደ፤፡ ከላይ እስከታች ያለው አመራር ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ትልቅ ትኩረት ሰጥቶት መሥራት በመቻሉ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ ተናግረዋል።

በተመዘገበው ውጤት በተለይም አርሶ አደሩ የበለጠ መነሳሳትን ፈጥሮለታል ያሉት አቶ ከበደ፤ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከዓመት ዓመት መሻሻል ማሳየት የቻለው አጠቃላይ የአመራሩንና የአርሶ አደሩን ግንዛቤ ማሳደግ በመቻሉ እንደሆነ አመልክተዋል።

እንደ አቶ ከበደ ገለጻ፤ ወደ በጋ መስኖ ሥራ ያልገቡ ክልሎችንም ወደ መስኖ ሥራ በማስገባት፣ በሰርቶ ማሳያ፣ በልምድ ልውውጥ፣ በአርሶ አደር ማሳ ላይ በተደረጉ የመስክ ጉብኝቶችና ሌሎች ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። የግብዓት አቅርቦትን ተደራሽ በማድረግ ረገድም የአፈር ማዳበሪያ፣ ኬሚካልና ምርጥ ዘርን ጨምሮ የተለያዩ ግብዓቶችን ለአርሶ አደሩ በቶሎ ተደራሽ በማድረግ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከዓመት ዓመት ውጤት ማስመዝገብ ተችሏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በግብርናው ዘርፍ የታዩ ውጤቶች የስኬታማነት ማሳያዎች ናቸው!

ግብርና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና 120 ሚሊዮን የሚጠጋውን ሕዝብ የሚመግብ ዘርፍ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ 96 ሚሊዮን ወይም 80 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ኑሮው ቀጥታ ከግብርና ስራ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከውጭ ምንዛሬ አንጻርም ብንመለከተው አብዛኛው ገቢ የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው፡፡

ይህንኑ ሃቅ በመገንዘብ በተለይ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል፡፡ የሀገሪቱን መልክዓ-ምድርና የአየር ጸባይን መሰረት ያደረጉ ስራዎች በመሠራታቸው ጤፍን የመሳሰሉ ምርቶች ምርታማነት ከመጨመሩም ባሻገር ኢትዮጵያ በታሪኳ አምርታቸው የማታውቃቸው የበጋ ስንዴና ሩዝን የመሳሰሉ ሰብሎች ከራስ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገበያም ለመቅረብ ችለዋል፡፡

ጤፍ በርካታ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ የሚመገበው እና አብዛኛውን የእርሻ መሬት የሚሸፍን ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት ይሄ ነው የሚባል የምርት ዕድገት ሳያሳይ ቆይቷል፡፡ የለውጡ መንግስት እውን እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ በአጠቃላይ የነበረው ዓመታዊ ምርት ከ300 ሚሊዮን ኩንታል ብዙም የዘለለ አልነበረም፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት ጤፍን በክላስተር ማረስ በመቻሉ ምርቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓመታዊ ምርቱ 639 ሚሊዮን ኩንታል ሊደርስ ችሏል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በአዲስ የልማት ጎዳና እንድትራመድ ካደረጓት የግብርና እንቅስቃሴ አንዱ የስንዴ ልማት ነው፡፡ ቀደም ሲል በጥቂት መጠን፤ በተወሰኑ አካባቢዎች፤ በክረምት ብቻ ይመረት የነበረውን የስንዴ ልማት ወደ በጋም በማሸጋገር የስንዴ ምርትን ከራስ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያም የማቅረብ አቅም ላይ ተደርሷል፡፡

የስንዴ ምርት በ2014/15 ዓ.ም የምርት ዘመን ወደ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ማሳደግ የተቻለ ሲሆን በሄክታር ሁለት ቶን ይገኝ የነበረው የስንዴ ምርትም ወደ አራት ቶን ማሳደግ ተችሏል፡፡

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በ2016 ምርት ዘመን ወደ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማምረት እየተሠራ ነው፡፡ አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት ቀዳሚ ስንዴ አምራች ለመሆን በቅታለች፡፡ በ2015 ዓመት ብቻ 32 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ መቅረቡ የዚሁ ስኬት አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክ በትኩረት በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከተውም በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በሩዝ መልማት የሚችል መሬት ቢኖርም በየዓመቱ ከ200 ሺህ ቶን በላይ ሩዝ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ 200 ሚሊዮን ዶላር ወጭ ታደርጋለች፡፡

ሆኖም በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ስርዓት መተግበር ከጀመረ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ፊቱን ወደ ሩዝ ምርት በማዞር በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል፡፡ በተለይ በአማራ ፎገራና በጅማ አካባቢዎች እየተከናወነ ያለው የሩዝ ምርት ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይ ሀገርነት ወደ ላኪነት የሚያሸጋግራት ነው፡፡

የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ከ35-40 በመቶ የሚሸፍነው ቡናም ምርታማነቱ ጨምሯል፡፡ 500ሺ የነበረው ዓመታዊ ምርትን ወደ 800 ሺህ ማሳደግ ተችሏል፡፡ በዚህም 700ሚሊዮን ዶላር የነበረው የውጭ ገቢ ወደ 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ ችሏል፡፡ የሻይና ቅመማ ቅመም ዘርፍን ምርታማነት ማሳደግ በመቻሉ ለሀገሪቱ እስከ 20 ሚሊዮን ዶላር የማምጣት አቅም ላይ ደርሷል፡፡

ከዚህ በሻገርም በሌማት ትሩፋት ንቅናቄ በሁሉም ክልሎች ከፍተኛ ምርታማነት ታይቷል። በማር፤ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋጽዖ፣ በጓሮ አትክልትና በፍራፍሬ ምርት ላይ የጎላ ለውጥ መጥቷል። በዚህም ዜጎች እየተፈጠረ ያለውን የዋጋ ግሽበት እንዲቋቋሙ፣ ተጨማሪ የሥራ ዕድል እንዲያገኙና ብሎም ከራሳቸው ተርፎ ለገበያ እንዲያቀርቡ አስችሏል።

በአጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ ያለው መሻሻል ስንዴን፤ ሩዝንና አቦካዶን የመሳሰሉ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ አልፎ ለውጭ ገበያም እንዲቀርብ ያደረገ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር የተመሰከረለትና ኢትዮጵያም በግብርናው ዘርፍ እምርታ እያሳየች መምጣቷን የሚመሰክር ነው !


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሆስፒታሊቲ ዓውደ ርዕይ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ከተሞችም ቢቀጥል !

ሚሊዮን ሺበሺ

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የቱሪዝም ገቢያ ቸው ከአጠቃላይ ገቢያቸው ከ50 በመቶ በላይ የሆኑ ሀገራት ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ የእነዚህ አገራት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መዳረሻ ሲታይ ግን ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት አቅም እዚህ ግባ የሚባል ላይሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

በተቃራኒው ኢትዮጵያ ሊለማ የሚችል ከፍተኛ የሆነ የቱሪዝም አቅም፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት ሆና ከዘርፉ የምታገኘው ገቢ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምን እንዲህ ሆነ ከተባለ ምንም ውስብስብ ጥናት ሳያስፈልገው የቱሪዝም ሀብታችንን በአግባቡ አለማወቃችን፤ አለማልማታችንና አለማስታዋወቃችን እንደሆነ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም፡፡ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ልምዳችን አለማደግም ከዚሁ ጋር አብሮ የሚነሳ ነው፡፡

ይህንን ችግር በተወሰነ መልኩ ይቀርፈዋል፤ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምንም ያነቃቃል በሚል ባለፈው መስከረም 29 ቀን 2016 ዓ.ም በቱሪዝም ሚኒስቴር አዘጋጅነት የቱሪዝም ሆስፒታሊቲ ዓውደ ርዕይ በሳይንስ ሙዚየም ተከፍቷል፡፡ ይህ ዓውደ ርዕይ ለአንድ ወር ያህል ቆይቶ እነሆ የፊታችን ረቡዕ ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም ይጠናቀቃል፡፡ ለመሆኑ ዓውደ ርዕዩ በአንድ ወር ቆይታው ምን መነቃቃት ፈጥሮ ይሆን? የሚለውን የዛሬ አጀንዳዬ ማጠንጠኛ ነው፡፡

የዓውደ ርዕዩ የመክፈቻ ዕለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መገኛታቸውና፤ መልዕክት ማስተላለፋቸው በራሱ አንድ መነቃቃት መፍጠሩን መገመት የሚከብድ አይደለም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ በስፍራው መገኘት በራሱ ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠት አንድ አቅም የሚፈጥር ነውና።

በዓውደ ርዕዩ የተካተቱ የሀገሪቱ ባሕላዊ እና ታሪካዊ ቅርጾች /በየክልሎች የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶች፣ ባሕላዊ መገልገያዎች፣ የተለያዩ ባሕላዊ መገለጫዎች፣ የየአካባቢው ታሪካዊ ማስታወሻዎች /፤መልካ ምድራዊ ውበቶች አንድ ሰው አንድ ቦታ ሆኖ ኢትዮጵያን በዘርፉ ያላትን ሀብትና እምቅ አቅም ማሳየት ያስቻለ ነው። ይህ በጎብኚው ውስጥ ሊፈጥር የሚችለው መገረምና መደመም በስፍራው በመገኘት ብቻ ማግኘት የሚቻል ነው።

በስፍራው ጀጎል ግንብ፣ የአክሱም ሀውልት፣ የላሊበላ ፍልፍል አብያተ ክርስቲያን የመሳሰሉት ቅርሶች በወካይ ሞዴሎቻቸው ይታያሉ፡፡ የተፈጥሮ መስህቦች (ሜዳና ተራራው) ሳይቀር በአምሳላቸው ይታያሉ፡፡ በእያንዳንዱ ቦታ ላይ ያሉ ማብራሪያ የሚሰጡ ሰዎች ደግሞ ረቂቅ በሆኑ ነገሮች ላይ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

የመክፈቻው ዕለት እንደተገለጸው፤ የአውደ ርዕዩ ዓላማ በኢትዮጵያ የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን፣ የማሕበረሰቡን ታሪክና ልዩ ልዩ ባሕሎች ማስተዋወቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ምን ያህል ተሳክቷል ከተባለ፤ ምንም እንኳን ሙሉ እውነታውን የሚያውቀው አዘጋጁ አካል ቢሆንም እንደ ተመልካች ግን ያስተዋልኩትን መመስከር የምችል ይመስለኛል፡፡

በተለይም እንደተከፈተ በነበሩት ሳምንታት አውደ ርዕዩ ብዙ ታዳሚዎች ነበሩት፡፡ በሁሉም የመጎብኛ ቦታዎች ከልጅ እስከ አዋቂ፤ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩንቨርሲቲ ተማሪ በስፋት ተጎብኝቷል፡፡ ሥራዬ ብለው የሚሄዱ ጎብኝዎች ነበሩ፡፡

መገናኛ ብዙኃን እስከዚህ ሳምንት ድረስ ሲሰሯቸው በነበሩ ዘገባዎችና ፕሮግራሞች ላይ እንዳስተዋልኩት በየቀረጻው ቅጽበት ብዙ ታዳሚዎች ነበሩ፡፡ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ የብዙ ተቋማት ሰራተኞች በቡድን በቡድን ሲጎበኙ ታይቷል፡፡ በቤተሰብ ደረጃ ፕሮግራም ይዘው ቅደሜና እሁድ ልጆቻቸውን ያስጎበኙ የነበሩ ወላጆች እንደነበሩ አስተውያለሁ፡፡

በእርግጥ በከተማዋ ነዋሪዎች ውስጥ እንዲህ አይነት መነቃቃት የተፈጠረው የቱሪዝም ጉዳይ ሀገራዊ አጀንዳ በመሆኑ ነው፡፡ የሳይንስ ሙዚየም በራሱ ለአውደ ርዕዩ ልዩ ውበት መጎናፀፉም አይካድም፡፡

ዓውደ ርዕዩ የፈጠረው ሌላው መነቃቃት ደግሞ ብዙ ሰዎችን ከዋናዎቹ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የመሄድ መነሳሳት መፍጠሩ ነው፡፡ ለማሳያነት የተቀመጡ ቅርሶችን ያስተዋለ ሰው ‹‹ዋናውን ቢያዩት እንዴት ሊሆን ነው?›› የሚል ስሜት የፈጠረበት ይመስላል፡፡ ከዚህ በመነሳትም እስካሁን ቅርሶቹን ባለማየቱ የመጸጸት ስሜት የተሰማቸው እንዳሉም ታዝቤያለሁ፡፡

በነገራችን ላይ በብዙዎች አመለካከት ‹‹ቱሪስት›› ሲባል ወደ አዕምሯቸው የሚመጣው የውጭ አገር ዜጋ ነው፡፡ ቱሪስት ማለት የውጭ አገር ዜጋ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ ዝርዝሩ ይቅርና ቱሪስት ማለት በአጭሩ የሆነን ቦታ የሚጎበኝ ሰው ማለት ነው፡፡ ከሐረር ሄዶ ፋሲል ግንብን የሚጎበኝ ኢትዮጵያዊ ቱሪስት ነው፡፡ ከጎንደር ሄዶ የሐረር ግንብን የሚጎበኝ ጎንደሬ ቱሪስት ነው፡፡ ከወለጋ ሄዶ አክሱምን የሚጎበኝ ሰው ቱሪስት ነው፡፡

እንዲያውም በአንድ የቱሪዝም ውይይት ላይ የሰማሁት አንድ አስተያየት ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ያለው ከውጭ በሚመጡ ዜጎች ነው፡፡ የአገር ውስጥ ቱሪስት እንቅስቃሴ ባሕል አልተደረገም፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ቱሪዝም ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ከአራት ዓመት በፊት የተሰራ ጥናት እንደሚያመለክተው፤ የአገር ውስጥ ጎብኚ ሚና በሚገባ አልተጠናም፤ ለዚህ ምክንያቱም አብዛኞቹ ጥናቶች የሚያተኩሩት በዓለም አቀፍ ጎብኚዎች ላይ ስለሆነ ነው፡፡

እንደ አንዳንድ ጥናቶች ከሆነ ፤ በአፍሪካ ብሎም በኢትዮጵያ የአገር ውስጥ ጉብኝት ያለበት ደረጃ ደካማ ነው፡፡ ለአገር ውስጥ ጉብኝት መዳከም ምክንያት ተብለው በጥናቱ ውስጥ ከተጠቀሱት አንዱ የአገር ውስጥ ጉብኝት የስትራቴጂ ዕቅድ አለመኖር ነው፡፡ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን የሚመለከቱ አሰራሮች የውጭ አገር ጎብኝዎችን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸው ነው፡፡

በጥናቶቹ ሌላው እንደ ምክንያት የሚጠቀሱት፤ አካባቢያዊ ግጭቶች ናቸው፤ እነዚህን ግጭቶች የሚቀሰቅሱ የመገናኛ ብዙኃን /በተለይም የማሕበራዊ ድረ ገጾች/ ግጭቶቹ ብሄር ተኮር ዕይታ እንዲላበሱ ማድረጋቸው ነው፡፡ ስለ ግጭቶቹ የሚፈጠሩ ትርክቶች አንዳንድ አካባቢዎች በመጥፎ እና በአስፈሪ ገጽታ እንዲሳሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ትርክቶቹ የሚፈጥሩት ፍርሃት የአገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ሌላው በዋነኛነት ጥናቶቹ የሚጠቅሱት ምክንያት የተለመዱት የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ ብቻ ሙጭጭ ማለትን ነው፡፡ ይህም አዳዲስ የቱሪስት መደራሻዎችን ከማስተዋወቅ ይልቅ ቀደም ሲል የተዋወቁ ላይ እውቀትን እና ሀብትን የማባከን ችግር ነው።

በአጠቃላይ፤ ለቱሪዝም ያለን አመለካከት አለማደግ እና የአገር ውስጥ ጉብኝት ባሕላችን በጣም ደካማ መሆን በዘርፉ የሚጠበቀውን ያህል ተጠቃሚ እንዳንሆን አድርጎናል። ይህንን ሀገራዊ እውነታ በመቀየር ዘርፉ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚኖረውን ድርሻ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል። ለዚህም ለቱሪዝም ያለንን እይታ እናሳድግ፤ ለአገር ውስጥ ጉብኝት ትኩረት እንስጥ። በአዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየም የተደረገው የቱሪዝም ሆስፒታሊቲ ዓውደ ርዕይ በዘርፉ እየፈጠረ ካለው መነቃቃት አንጻር፤ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ ከተሞችም የሚቀጥልበት ሁኔታ ይመቻች!።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የወደብ ጉዳይ!

ሳንዱዘር አሥራት
ጋዜጠኛ እና ሲኒየር የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ

ከሦስት አሥርት ዓመታት በላይ ተዳፍኖ የቆየው የኢትዮጵያ የባሕር በር መውጫና የወደብ ተጠቃሚነት ጉዳይ ዛሬም ከውስጥ የሚመነጭ መፍትሔን የሚሻ ሆኖ ይስተዋላል። የቀይ ባሕር ክልል የዓለማችን አሥራ ሁለት ከመቶ (12%) ልዩ ልዩ የንግድ እንቅስቃሴ የሚከናወንበት በባሕር ላይ ንግድ ድርጅቶች በየግዜው ይፋ ከሚያደርጉት መረጃ ለማወቅ ይቻላል። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አንስቶ የምዕራብና ምስራቅ አውሮፓ ሀገራት፤ የሩቅና መካከለኛ ምስራቅ ሀገራትን ጨምሮ አሜሪካ በቀጠናው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ብልጫን ለማግኘት ባልተቋረጠ መልኩ ብርቱ ፉክክር እያደረጉ መሆኑ ይታወቃል።

የቅኝ ግዛት ዘመንን ጨምሮ ልዕለ ሃያላን ሀገራት የቀይ ባሕር ክልል ሕዝቦችና ሀገራትን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ፈጽሞ ከግምት ውስጥ ያላስገባ እንቅስቃሴ በቡድንና በተናጠል በስፋት ሲያደርጉ ይስተዋላል። በአካባቢው በሁሉም ረገድ በልጦ ለመውጣት የሚያደርገው ፍትሃዊነት የጎደለው ፉክክርና ፍጥጫ የቀጠናው ሀገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውን እንዲያጡ እያስገደደ ያለ ከመሆኑም ባለፈ ለብሔራዊ የፀጥታ ስጋት ተጋላጭ እንዲሆኑም አድርጓቸዋል።

በቀጠናው እየተደረገ ያለው የልዕለ ሃያላኑ ሁሉን አቀፍ በየደረጃው የሚገለጽ ብርቱ ጫና የቅኝ ግዛት አርተፊሻል ድንበር፣ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ያረጀ ያፈጀ አስተሳሰብና በቀጠናው አገራት ሕዝቦች መካከል ኃይማኖትን ጨምሮ ያሉ ተፈጥሯዊ ልዩነቶችን በአሉታዊ መንገድ አጉልቶ አንዱን ለሌላው ስጋት አስመስሎ በማሳየት የሚደረግ ነው። አንዱ ለሌላው የሁለንተናዊ ጥንካሬው ምንጭ መሆኑ ቀርቶ ጠላት እንደሆነ በማስመሰል፤ ከፋፍሎ አቅም በማሳጣት ላይ የተመሰረተ የራስን ጥቅም ብቻ ማዕከል የሚያደርግ የተበላሸ የውጭ ግንኙነት ፖሊስ የሚከተሉ መሆናቸውን የአካባቢው የጂኦ-ፖለቲካ ተመራማሪዎች አጽንኦት ሰጥተው በየመድረኩ ሲናገሩ ይደመጣል።

ይህም ነጣጥሎ ኃይልና ተደማጭነትን የማሳጣት የልዕለ ሃያላኑ እንቅስቃሴ የቀጠናው ሀገራቱ ጠንካራ ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ውህደትና የፖለቲካ መተማመን እንዳይኖራቸው አድርጓል ብለው የሚናገሩ ምሁራንም እጅግ በርካታ ናቸው። በፈረንጆች ኖቬምበር 17/1869 በግብጽ የባህር ክልል በኩል የተሰራው፣ ቀይ ባሕርን በቀጥታ ከሜድትራኒያን ባሕር ጋር የሚያገናኘው ሰው ሰራሽ "ስዊዝ ካናል "የተሰኘ የውሃ ውስጥ መሿለኪያ መገንባቱ ደግሞ የአካባቢውን የስበት ማዕከልነት በእጅጉ ከግዜ ወደ ግዜ እያሳደገ እንደሚገኝ በፍጥነት ከሚለዋወጠው የቀጠናው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ተጨባጭ ሁኔታና ታሪክ መረዳት ይቻላል።

የመሿለኪያው መከፈት አፍሪካን እንዲሁም የምስራቁን የአህጉሪቱን ክፍል ከመካከለኛና ሩቅ ምስራቅ ሀገራት፤ ከምዕራብና ምስራቅ አውሮፓ ሀገራት እንዲሁም አሜሪካ በቀላሉ የሚያገናኝ መሆኑ የአካባቢውን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ በእጅጉ ከፍ ያደረገም ነው።፤ ከቀጣናው ውጭ የሚገኙ ልዕለ ሃያላን ሀገራት በየደረጃው የሚገለጽ የኢምፔሪያሊዝምና የኒዮ ኮሎኒያሊዝም መልክ ያለው ቀጠናውን ለፖለቲካ አለመረጋጋትና ለሽብር አደጋ ስጋት የሚዳርግ ፉክክር እንዲያደርጉም ምክንያት የሆነ ታስቦ ተግባራዊ የተደረገ ፕሮጀክት ነው።

ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ረገድ የመሿለኪያው መከፈትን ጨምሮ ቀይ ባሕር በመርከብ ልዩ ልዩ ነዳጅና ዘይቶችን፤ ሃይድሮካርበን፣ ልዩ ልዩ ሸቀጥና የፍጆታ ምርቶችን፤ ሌሎችንም የጦር መሳሪያን ጨምሮ ግዙፍ ቁሳቁሶችን ወደ ሦስቱም አቅጣጫ 193 ኪሎ ሜትር በሚረዝመው መሿለኪያ አማካኝነት በፍጥነት ማለትም ወደ አውሮፓ፣ ኢዥያና መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ማጓጓዝ እንዲቻል አቅም የፈጠረም ነው። መሿለኪያው በዓመት 30 ኮንቴይነር ምርቶች ግብይት እንዲከናወን በማስቻሉ USD $1 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ገቢ በማመንጨት የሀገራቱን ኢኮኖሚ ከመደገፉም ባሻገር የቀጠናው እስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ጎልቶ እንዲታይም አድርጓል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እንደ ግብጹ የስዊዝ ካናል አስተዳደር መረጃ በፈረንጆች 2020 ከ19,000 በላይ መርከቦች መሾለኪያውን ተጠቅመው በቀጠናው ጉዞ ማድረጋቸው ይፋ የተደረገ ሲሆን፤ በተመሳሳይ በቀን 50 መርከቦች እንዲሁ መሿለኪያውን ተጠቅመው ወደ መዳረሻቸው በማቅናት 3-9 USD $ ቢሊዮን የካርጎ ግብይት የምስራቅ አፍሪካ የባህር ክልልን ጨምሮ የተፈጸመ መሆኑን አመላክቷል።

**በሁለቱም ሀገራት ለሚኖሩ ወንድማማች ሕዝቦች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና ቀጠናዊ ትብብር ተጨባጭ አቅም ይሆን ዘንድ ከግጭትና ጦርነት በመለስ ያሉ ሌሎች የመፍትሔ አማራጮችን በመፈለግ ዘላቂ ሰላምን በቀጠናው ማረጋገጥ ከሁሉም የሚጠበቅ ነው**

በ1983 በሀገሪቱ የተደረገውን የመንግሥትና የፖለቲካ ስርዓት ለውጥን ተከትሎ ሕዝብን ለውይይት ባልጋበዘ/ ዕድል ባልሰጠ ፖለቲካዊ ውሳኔ ሀገሪቱ በታሪክ የእርሷ እንደነበሩ በግልጽ ተመዝግበው የተቀመጡና ለዘመናት ስትጠቀምባቸው የነበሩ ሁለት ወደቦቿን ጨምሮ የባሕር በር መውጫዋን እንድታጣ ያስገደደ ብሎም የመጪው ትውልድን ጥቅም ያላገናዘበ አሳዛኝ ውሳኔ ተላልፏል። በወቅቱ ተላልፎ የነበረው የፖለቲካ ውሳኔ የሁለቱን ሀገራት ዘላቂ ጥቅም የማያረጋግጥ የጥቂት ተፋላሚ ቡድኖች ፍላጎት ብቻ መሆኑ በበርካቶች ዘንድ ተደጋግሞ ሲነሳ የሚስተዋል ነው። በሁለቱም ሀገራት ለሚኖሩ ወንድማማች ሕዝቦች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና ቀጠናዊ ትብብር ተጨባጭ አቅም ይሆን ዘንድ ከግጭትና ጦርነት በመለስ ያሉ ሌሎች የመፍትሔ አማራጮችን በመፈለግ ዘላቂ ሰላምን በቀጠናው ማረጋገጥ ከሁሉም የሚጠበቅ ነው።

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ በቀዳማዊ አጼ ኃይለስላሴ ዘመን በቀይ ባሕር የውሃ ክልሏ ላይ አቋቁማው የነበረው የባሕር ኃይል በቀጠናው ያላትን ተደማጭነትና ብሔራዊ ጥቅም በአስተማማኝ ሁኔታ ማስከበር እንዲያስችላት ሲያበረክት የነበረው አስተዋጽኦ በእጅጉ ከፍተኛ እንደሆነ የሚነገር ቢሆንም ከ1983 የፖለቲካ ውሳኔ በኋላ እንዲፈርስ በመደረጉ ሳቢያ በአጠቃላይ ሰላምና ደህንነቷ ላይ ስጋት የሚፈጥሩ በቀጠናው የሚስተዋሉ ተለዋዋጭ አዳዲስ ክስተቶችን ለመቆጣጠር አዳጋች እንደሆነባትም ተያይዞ ይነሳል።

ከሦስት አሥርት ዓመታት ለሚበልጥ ግዜ ምንም ዓይነት አማራጭ መፍትሔ ከውስጥም ይሁን ከውጭ ባልተገኘበት ሁኔታ ሀገሪቱ በር ተከርቸም ተዘግቶባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማውጣት የጅቡቲን የወደብ አማራጭ እየተጠቀመች የምትገኝ መሆኗ የሚታወቅ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዓርብ ጥቅምት 2/2016 ምሽት፤ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በተላለፈውና ‹‹ከጠብታ ውኃ እስከ ባሕር ውኃ›› በሚል ርዕሰ ጉዳይ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ባደረጉት ማብራሪያ፤ "ዓባይና ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ተደርገው መወሰድ እንደሚኖርባቸው ያመላከቱት " ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በፍጥነት እየጨመረ ካለው የሕዝብ ብዛት ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ የባሕር በር መውጫ የግድ እንደሚያስፈልጋት ዝርዝር እውነታዎችን ለምክር ቤት አባላት ለቀጣይ ውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ ማብራሪያ መስጠታቸው የሚታወስ ነው ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም በማብራ ሪያቸው፤ "የቀይ ባሕርን ጉዳይ እኛ እንዴት ነው የምንመለከተው? ምንድን ነው እሳቤያችን? ይሄ እሳቤያችን ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ያዋጣል ወይስ አያዋጣም? መሆን አለበት ወይስ መሆን የለበትም? በሚለው ጉዳይ ላይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከስሜት ነጻ በሆነ መንገድ አስልቶ፤ ለልጆቹ መልካም ነገር መተው አለበት" ያሉ ሲሆን፤ "በሕዳሴና በተከዜ ጉዳይ እየተወያየን በቀይ ባሕር ጉዳይ አንነጋገርም ማለት የሚቻል አይሆንም" በማለት የምክር ቤት አባላት ወርደው በየደረጃው ሕዝብን የማወያየት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የጠየቁ መሆናቸውም አይዘነጋም።

የኢፌዴሪ መንግሥት ከለውጡ ማግሥት አንስቶ የባሕር ኃይል እንደገና ማደራጀትን ጨምሮ ሀገሪቱ የወደብ አማራጭና የባሕር በር መውጫ/መተንፈሻ ማግኘት በምትችልበት ሁኔታ ላይ ከጋዜጠኞች፣ ከባለሀብቶች፣ ከፖለቲከኞችና ምሁራን እንዲሁም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ከውስጥ የሚመነጩ አማራጭ የመፍትሔ አሳቦች ዙሪያ ተደጋጋሚ ምክክሮችን ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም በአንዳንድ አካላት መንግስት የውስጥ ጉዳዮችን በዚህ ለመተካት እንዳመጣው አጀንዳ ተደርጎ የሚናፈሰው መሰረተ ቢስ አሉባልታ ተቀባይነት የሚኖረው አይሆንም ፡፡

ከቀይ ባሕር ፍትሀዊ ተጠቃሚነትና በጋራ መልማት ጋር በተገናኘ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው አጀንዳ መነሻው ውይይት፤ መድረሻው የጋራ ተጠቃሚነት ነው። ታሪክና አስቀድሞ የነበረን መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ መሠረት ባደረገ መልኩ በአገር ወስጥ የሚደረግ ውይይትን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸው ወሰን ተጋሪ ሀገራት በጋራ በሚያደርጉት አካታች ንግግር የቀጠናውን ሁለንተናዊ ሰላም በዘላቂነት ለማስጠበቅ የሚያስችል መፍትሔ ማዋለድ እንደሚቻል በብዙሃን ተቀባይነት ይኖረዋል።

በቀጠናው እውን እንዲሆን የሚፈለግ የጋራ ተጠቃሚነት ጉዳይ በአንድ ሀገር የበላይነት ወይንም በተወሰኑ ቡድኖች ፍላጎት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ሁሉንም ወሰን ተጋሪ በቀጠናው የሚገኙ ሀገራትን ማዕከል በሚያደርግ አብሮ በወንድማማችነት የመልማት መርህ የሚወሰን ይሆናል።

ለዚህም ኢትዮጵያ ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ መጀመር አንስቶ እስካሁን ባለው ከታችኛውና ላይኛው የተፋሰስ አገራት ጋር በዘላቂነት እያደረገች ያለው ውይይት ሀገሪቱ በጋራ ተጠቃሚነትና መርህ የምታምን መሆኑን የሚያሳይና በቀጠናው እንደአብነት ልጥቀስ የሚችል ሁሉንም አካላት የሚያግባባ ምሳሌያዊ ተግባርም ጭምር ነው።

አስቀድሞ የሀገሪቱ ሉኣላዊ ግዛት ከነበሩ ሀገራት ጋር በየደረጃው የሚገለጽ ለፖለቲካዊ ውህደት መንገድ የሚጠርግ የኢኮኖሚያዊ ውህደት ሥራዎች- ማለትም እንደ አብነት የመሰረተ-ልማት ዝርጋታ ሥራ አብሮ ልታይ የሚገባ ነው።

ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ክልል ከጅቡቲ፣ ከኬንያ፣ ሶማሌ ላንድና ኤርትራ ወደቦችን መመልከትን ጨምሮ ከኤደን ባህረ -ሰላጤ ሀገራት ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በማጠናከር በቀጠናው መልማት የሚችሉ የወደብ አማራጮችን አቅም በሚፈቅደው ሁሉ መጠቀም እንድትችል መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ እንጂ ለመንግሥት ብቻ በአደራ የሚተው አይሆንም።

በውይይት የዳበሩ አዋጭ አማራጮች በየደረጃው ተግባራዊ በማድረግ አገሪቱ በቀጠናው አስቀድሞ የነበራትን ተቀባይነትና ተጽዕኖ እንዲሁም የባሕር -በር ወሰን ወደነበረበት እንዲመለስ ለማስቻል የውስጥ አንድነትን ማጠናከር፣ ከጠመንጃ በመለስ በሁሉም ረገድ የንግግር ባሕል እንዲዳብር በጋራ መስራትን ጨምሮ ጥንት በአገሪቱ ታሪክ ዜጎች በወንድማማችነት መፈጸም እንደቻሉት አኩሪ ገድል ሁሉ ለብሔራዊ ጥቅሞቻችን መከበር በዓለም አደባባይ በአንድነት መቆም እንደሚጠበቅብን ቀጠናዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።


### እንደ መውጫ

ለዓመታት ከዐባይ ግድብ ግንባታ መጀመር ጋር በተጓዳኝ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር ስናደርግ እንደነበረው ድርድር ሁሉ የቀይ ባሕር መውጫና የወደብ አማራጮችን አስፍቶ የመመልከት ጉዳይን በሚዲያ፣ በየደረጃው በሚደረጉ የሕዝብ፣ የምሁራንና የፖለቲካ ድርጅቶች ውይይት በሁሉም ዘንድ አጀንዳው ጎልቶ እንዲታይ ማስቻልን ጨምሮ በቀጠናው የሚገኙ ወንድማማች ሕዝቦችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አካታች መፍትሔ ማዋለድ እስኪቻል ድረስ በሁሉም ረገድ የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። አጀንዳው አድጎና ጎልብቶ ከቀጠናው አልፎ የዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ይታይ ዘንድ በየደረጃው አካታችና አዋጭ የዲፕሎማሲ አማራጮችን በመከተል ሀገራት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንዲያደርጉ ማግባባት አብሮ ሊከናወን የሚገባው ሌላኛው ዋነኛ ተግባር ነው !

# ወቅታዊ

# «የባሕር በርና የወደብ ጉዳይ ጊዜውን ጠብቆ የመጣ ትክክለኛ አጀንዳ ነው»

- አቶ ጥላሁን ከበደ
የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር



አስቴር ኤልያስ

አቶ ጥላሁን ከበደ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ባሉ ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሠርተዋል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በአዲስ መልክ በተደራጀው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሆነው ተሹመው ሥራ ጀምረዋል፡፡ አዲስ ዘመንም አዲሱ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አወቃቀሩን በተመለከተ እና በወቅታዊ የሀገሪቱ ሁኔታን አስመልክቶ ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ባሉ የተለያዩ ከተሞች ውስጥ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች መቀመጫ እንዲሆኑ መደረጉ አንድም ለከተሞቹ እድገት አንድም ፖለቲካዊ መረጋጋት እንዲኖር ታስቦ እንደሆነ ይነገራልና በእርስዎ አተያይ ይህ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጥላሁን፡-** በቅርቡ ምሥረታውን ያካሔደው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ስድስት ማዕከል እንዲኖረን ታስቦ የተወሰነ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በቀድሞው የደቡብ ክልል ውስጥ የነበሩ ዞኖች በክልል እንደራጅ ጥያቄያቸው ከዕለት ወደዕለት እየጎለበተ መምጣቱ የሚታወስ ነው፡፡ በበርካታ ዞኖች የተነሳ ጥያቄ የራሱ የሆነ ገፊ ምክንያት ኖሮት ወደፊት የመጣ መሆኑ እውን ነው፡፡

በተለይ የክልል ተቋማት በአንድ ማዕከል ላይ መሰባሰባቸው በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ አሳድሮም ነበር፡፡ ከዚህ አኳያ የከተሞች እድገት ላይም ሆነ የተጠቃሚነት ጉዳይ ላይ ችግር ፈጥሮ በመክረሙ ዞኖች በክልል እንደራጅ የሚለውን ጥያቄ አጉልተው ሲጠይቁ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በተደጋጋሚ ከሕዝቡ ይነሳ የነበረው ሌላው ምክንያት የቀድሞው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አልጠቀመንም፤ አላሳተፍንምም የሚል ጭምር ነበር፡፡ የፍትሐዊ ተጠቃሚነት፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲሁም በቅርበት አገልግሎት ለማግኘት አልቻልንም የሚልም ቅሬታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት በክልል እንደራጅ  የሚለው ጥያቄ አይሎ ሊመጣ ችሏል፡፡ በወቅቱም በየመድረኩ ሲነሳም ነበር፡፡

ይህ ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ምን መከተል ይሻላል በሚል ከሁሉም አካባቢ ከተውጣጣ ምሁር ጋር እንዲሁም የሕዝብ እንደራሴዎች በተገኙበት ምክር ቤት ውይይት አድርገናል። ውይይቱን ስናደርግ ሰብሰብ ብለን እንደራጅ፤ በየዞኑ ክልል እንዲሆን ያልነው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ስንመለከት ብዙም አቅም ያለው ስለማይሆን ኅብረት ፈጥረን ብንደራጅ የበለጠ አቅም ይኖረናል በሚል ተነጋገርን፡፡

ከዚህ  ቀደም በቀድሞው በደቡብ ክልል የነበሩ የታዩ ግድፈቶችን በሚያርም አግባብ ክልሉን ብናደራጅ መልካም ነው ወደሚለውም መምጣት ቻልን፡፡ ይህ በመሆኑም በክላስተር ሰብሰብ ብለን እንደራጅ፤ ነገር ግን መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎቻችን እንዲፈቱ የሚለውን ሕዝቡ ይሁንታ ስለሰጠው ክልሉን ስናደራጅ በመርህ ደረጃ ክልሉ ብዝሃ ማዕከላት እንዲኖር፤ ማለትም የብዝሃ ማዕከላት ከተሞች ደረጃም እኩል ደረጃ ያላቸው እንዲሆኑ በሚል ተስማማን፡፡

በእርግጥ እንደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ስድስት ማዕከላት እንዲኖር ማድረግ ብለን ስንስማማ ቀድሞም ቢሆን በሕገ መንግሥቱ ብዝሃ ማዕከላት ያለው ክልል እንደሆነ የሚታወቅ ነው። አንቀጽ ስድስት ላይ የክልሉ መቀመጫ ወይም ደግሞ የክልሉ ከተሞች ብዝሃ ማዕከል ያልናቸው ስድስት ከተሞች ናቸው ብለን ለይተናል፡፡ ከተሞችንም እንዴት እንምረጥ፣ መስፈርታቸውስ ምን መሆን አለበት ብለን ተወያይተንና ተነጋግረን ከተሞችንም መርጠናል፡፡

ከተሞቹ ሲመረጡ የክልሉ መቀመጫ ስድስቱም ከተሞች በእኩል  ደረጃ የክልሉ መቀመጫ እንዲሆኑ ስንወስንም በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካዊ ለከተሞችም ሆነ ለመላ ሕዝባችን ጠቃሚ ይሆናል ብለን በስፋት ገምግመን ነው፡፡

በዋናነት የሕዝቡ ተጠቃሚነት ለከተማ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ለሚገኙ ለአጎራባች ዞኖችም ጭምር ነው፡፡ በፊት አገልግሎት ወደተጠቃሚው ሕዝብ ማዳረስ ብዙም የሚቻል አልነበረም፡፡ ከዚህ የተነሳ በአንድ ማዕከል መሆኑን ለብዙ ነገር ሕዝቡ ርቆብናል ሲል ነበር፤ የክልል አመራሮች ሳናውቃቸውና ሳናያቸው ጊዜው ያልፋል በማለትም ሲናገር ነበር፡፡ ስለዚህ ወደአካባቢያችን ቀረብ ይበሉ፡፡

በቀድሞው ክልል አንድ ከተማ የክልል መቀጫ ሲሆን፣ ሁሉ የሚሰበሰበው ወደ አንድ ሴክተር ነው፡፡  አሁን ግን በስድስት ማዕከል ሲሆን፣ በዚህም ወደመላ ሕዝባችን በመድረስ ቀረብ ያለ አገልግሎት እንዲኖር አድርገናል፡፡ በዚህም አግባብ ይርቅብናል የተባለውን ችግር በዚህ መልኩ መፍታት ችለናል፡፡

ሁለተኛው የከተሞች ቁጥር ስድስት ስናደርግ ለከተሞችእድገትምየራሱየሆነአስተዋጽኦአለው። የክልል ማዕቀፍ ስለሆነ በልዩ ሁኔታ የዞንም፣ የወረዳም የከተማ አስተዳደርም በሦስትዮሽ ከተሞች እንዲያድጉ የራሱ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ስለዚህ የከተሞች እድገት በጣም የተራራቀ መሆን የለበትም፤ የተቀራረበ እንዲሆንም አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለብን፡፡ እነዚያ የክልል ማዕቀፍ የሆኑ ከተሞች ብቻ ሳይሆን በዙሪያቸው ያሉ ከተሞች ሁሉ እንዲያድጉ ይደረጋል፤ ስለዚህ የከተሞች እድገትና የከተሞችን ሁኔታ ከመቀየር አኳያ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። እነዚህ የሚታዩት በተለይ ከኢኮኖሚ አኳያ ነው፡፡

በማኅበራዊ ደረጃም በተለይ ስድስት ከተሞች የክልሉ መቀመጫ ሲደረጉ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በበለጠ እንዲጠናከር ያደርገዋል፡፡ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል 32 ብሔረሰቦች ያሉበት ነው፡፡ መላ ኢትዮጵያውያን የሚኖርበት ክልል ነው ማለትም ይቻላል፡፡ የክልላችን መርህ ብለን ያስቀመጥነው የሠላም ተምሳሌት፣ የእድገት ተምሳሌት የብልጽግና ተምሳሌት ብለን ነው፡፡

ብልጽግና ስንል የወንድማማችነትና የሠላም ነው፡፡ ክልላችን ደግሞ በርካታ ሕዝብ የሚኖርበት ክልል ነው፡፡ ከዚህ አኳያም የምንወስዳት ትንሽዋ ኢትዮጵያ በሚል ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የመቻቻል፣ ወንድማማችነት፣ መከባበርን በአግባቡ የምናይበት ክልል ነው፡፡ ስለሆነም ብዝሃ ማዕከልን ስናደርግ ይህንን በክልሉ ስም በተለይ አንድ ማዕከል ላይ ከሚሆን በርካታ ማዕከላት ማድረጋችን ሁሉም ሰው በአግባቡ አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርገዋል፡፡ ይህ የበለጠ ማኅበራዊ መስተጋብርን የሚያጠናክር እንደሆነ የተማመንበት ሁኔታ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህን ስታደርጉ ማዕከላቱ የተለያዩ ከተማ እንደመሆናቸው ለአገልግሎት አሰጣጣችሁ ችግር አይፈጥርም?**

**አቶ ጥላሁን፡-** ማዕከላቱ በተለያየ ከተማ መሆናቸው እንደተባለው የተለያየ ጥያቄ ሲነሳ እናስተውላለን፡፡ በተለይ ከአቅም ጋር በተያያዘ ወጪ እንደሚያስወጣም ይነገራል፡፡ እኛ ከዚህ ጋር በተያያዘ አስቀድመን የተለያየ ሥራ ስንሠራ ቆይተናል፡፡ ምክንያቱም በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች ላይ ማዕከላትን ማድረጉ ሙከራው አዲስም ስለሆነ እንዴት አድርገን ነው በአንድ ማዕከል ላይ ሲሰጥ የነበረውን አገልገሎት ስድስት ማዕከል ላይ ማድረግ የምንችለው? ተገልጋይ ሳይጉላላ አቅማችንን አሟጥጠን እና ወጪን ቆጥበን የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ምን ዓይነት መንገድ እንከተል? የሚለውን ለማወቅ የተለያዩ ጥናቶችን እያጠናቀቅን ነው፡፡

በእነዚህ ስድስት ማዕከላት ላይ ተገልጋይ ብዙ ሳይጉላላ በተለይ ደግሞ በተሻለ ሁኔታ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ የምንከተልበትን የአሠራር ሥርዓት ልናስኬድ ይገባል፡፡ ለዚህ አሠራር ያዘጋጀነው ሕግና ደንብ ጭምር ነው። ስድስቱም ማዕከላት የማዕከል አስተባባሪዎች ወይም ደግሞ በምክትል ርዕሰመስተዳድር ማዕረግና ምክትል ርዕሰመስተዳድሩ የሚመሩት ማዕከላትን ነው ያዘጋጀነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ማዕከላት አንድ ተገልጋይ አንድ ጊዜ ቢመጣ እዚያው ሆኖ ስድስቱን ማዕከላት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶችን ማግኘት የሚችልበትን ሥርዓት እንዘረጋለን ብለናል፡፡

ይህ በቴክኖሎጂም የታገዘ እንዲሆን ሥራውን ማቃለያ ዘዴ ተጠቅመን ለመሄድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት ዓለም ዘምና የደረሰችበትን ደረጃ መረዳት እምብዛም አይከብድም፡፡ ግሎባላይዜሽን ላይ ናት፡፡ ምክንያቱም እዚሁ ሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነን በመላ ዓለም ሥራዎችን ማካሄድ ተችሏል። ከዚህም በላይ ውስብስብ የሆነውን የጤናን ሁኔታ በዚሁ በኦንላይን የሚካሔድበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ስለዚህ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ደግሞም ሥርዓት ያለው እና በሕግ አኳያ የተደገፈ የአሠራር ሥርዓት ዘርግተን በዚያ አግባብ እንዲካሄድ ወስነናል፡፡

ስለዚህ በተቻለ መጠን ወጪ ቆጥበን የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት አድርገን በዚያ መንገድ እየተንቀሳቀስን ነው። ለዚህ ደግሞ በጋራ ሊሠሩ የሚችሉ አካላት እና አመራሩ ይህን መንገድ ተከተትለን እየሠራን እንገኛለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከአምስት ዓመት ወዲህ ከተመሠረቱ አዳዲስ ክልሎች መካከል ከሲዳማ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የምትቀስሙት ተሞክሮ አሊያም የምትማሩበት አካሔድ ይኖር ይሆን?**

**አቶ ጥላሁን፡-** እንደሚታወቀው የቀድሞው የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምንም እንኳን የሲዳማ ቀጥሎም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች እንደየቅደም ተከተላቸው ቀድመው የተደራጁ ቢሆንም እነሱን ጨምሮ ክልሉ በአሁኑ ወቅት አራት ክልል ሆኖ ተደራጅቷል፡፡

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የተደራጀነው በአንድ ቀን አንድ ላይ ነው፡፡ ቀድመው የተደራጁት ክልሎችን በወቅቱ አደራጅተን ወደሥራ እንዲገቡ አድርገናቸዋል፡፡ ከእነዚህ ቀድመው ከተደራጁ ክልሎች ከትምህርት አኳያ የወሰድናቸው አንዱና ትልቁ ነገር ሕዝብን በማነቃነቅ በተለይ ቃል የተገቡ ሥራዎችን በአግባቡ ያለመፈጸም፣ ሊሳካ የማ።ይችለውን ጉዳይ ቃል የመግባትና ክልል መሆን ማለት ሁሉ ነገር የተሟላ እንደሆነ ማሰብ ላይ ነው፤ ይህ ደግሞ በኋላ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ፈጥጠው ሲመጡ መልስ መስጠት የሚከብድ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱ ከሕዝቡ በኩል  የክልልነት ጥያቄን ያቀረብነው ለዚህ ነው ወይ? የሚል ነገር መምጣት ይጀምራልና እነዚህንም ጉዳዮች ጭምር መፍታት የሚቻለው የማንደርስባቸውን ሥራዎች እንደምንደርስባቸው አድርገን ከመናገር መቆጠብ ነው፡፡ ከልምድ አኳያ በጋራ ሕዝብን አስተባብረን ሕዝቡ ባለቤት ሆኖ ከመሥራት ያለፈ ሌላ የተለየ ነገር እንደሌለ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# «የባሕር በርና የወደብ ጉዳይ...

ከገጽ 7 የዞረ

በደንብ ይዘን ቀሪ የልማት ሥራዎችን የራሳችንን አቅም ራሳችን አንቀሳቅሰን መሄድ እንደሚገባን ነው፡፡

ከዚያ ውጪ የምንለው ነገር ቢኖር የክልል ምስረታ ብለን በዚያ ላይ መላ ኢትዮጵያውያን እና መላ የንግዱ ማኅበረሰብም ይሁን እንዲሁም ደግሞ መንግሥታዊ ድርጅቶች በሃሳብም ሆነ በሌላ ሌላውም የተወሰነ ድጋፍ በማድረግ ይህን ጊዜ እንሻገር ነው፡፡ በሌላ በኩል ጸጋዎቻችንን ማየት እና ከዚህ ቀደም ያልታዩ አቅሞቻችን ማየት ላይም እንሠራለን፡፡

ከደቡብ ምዕራብ የወሰድነው ልምድ ብዝሃ ማዕከላትን ቀድመው የጀመሩት እነርሱ ናቸው፡፡ ብዝሃ ማዕከላት በሕዝቡ ውስጥ የነበሩ ጥያቄዎችን ለመፍታት የሚያስችል መንገድ በመሆኑ ትክክል ነው ብለን ወስደናል፤ በመሆኑም ይህን ተሞክሮ እኛም መቀመር ችለናል፡፡ የሕዝቡን ፍላጎት ደግሞ ለማሳካት በየጊዜው አቅማችንን እያጎለበትን እንሄዳለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክልሉ አዲስ ሆኖ እንደመዋቀሩ ይህንኑ ተከትሎ አዳዲስ ዞኖችም ከወረዳ ደረጃ ከፍ ብለው ተካተዋል፤ በመሆኑም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ምናልባትም ከአጎራባች ክልሎች ጋር የተፈጠረ የወሰን ችግር አጋጥሟችሁ ከሆነ? ከሆነስ ለመፍታት እየሠራችሁ ያለው እንዴት ነው?**

**አቶ ጥላሁን፡-** የደቡብ ብሔር፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች ክልል አንድ ላይ በነበርንበት ጊዜ ክልል ሆነን የተደራጀነው አብዛኞቻችን ዞኖች ነን፡፡ በወቅቱ ዞኖች በክልል ስር በነበሩበት ጊዜ በተወሰነ መልኩ የወሰን እንዲሁም የግጦሽ መሬት ጉዳይ ጥያቄዎች አሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ለእኛ በተለይ ከወሰን ጋር ተያይዞ ለአራቱም ክልል በጣም ትልቅ አጀንዳ ነው፡፡ ነገር ግን የተነሳ ነገር የለም፡፡ ይሁንና ቢነሳ እንኳ የቀድሞው የደቡብ ክልል የሆንን በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወደአራት ክልል የተደራጀን በጋራ ተቀምጠን የምንፈታው ይሆናል፡፡

በአሁኑ ወቅት የሀብት ክፍፍልን እንኳ በተመለከተ ኮሚቴ ተቀምጦ እያየው ስላለ ይህ ነገር ቢከሰት የጋራ መድረክ ፈጥረን የምንፈታው ይሆናል፡፡ ለጊዜው ወጣ ያለ ከወሰን ጋር ተያይዞ የመጣ አጀንዳ ብዙም የለም፡፡ ይሁና ወደፊት ሊኖሩ ስለሚችሉ ሳይባባሱ ከወዲሁ እየተነጋገርንበት የምንሄድበት ይሆናል፡፡ ነገር ግን እንደሚታወቀው ዞኖች ከዚህ ቀደም የተደራጁ ናቸው። ስለሆነም አዲስ የሚፈጠርላቸው የወሰን ጉዳይ አይኖርም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ስተያዘው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ያልዎ አተያይ እንዴት ይገለጻል? እንደ ክልልስ የሚኖራችሁ ድጋፍ ምንድን ነው?**

**አቶ ጥላሁን፡-** በብሔራዊ ደረጃ እና ኢትዮጵያውያንን ብዙ አንድ የሚያደርጉን እና የምንጋራቸውን ነገሮች አሉን፡፡ ሊያግባቡን የሚችሉ ጉዳዮችም በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ነገር ግን ጥቂት የሚያለያዩን ጉዳዮች ትልቅ ቦታ ይዘው እርስ በእርስ ለመናቆር ምክንያት እየሆኑ ነው፡፡

እንደ ሰውኛ ባህሪ እኛ አሁን ፈተና የሆነብን እጅግ በጣም ብዙ አንድ የሚያደርገን ጉዳይ እያለ በጣት የሚቆጠር ጥቂት ነገር የግጭት እና ያለመግባባት መንስዔ እየሆነ መምጣቱ ነው፤ ታዲያ ለምን ይሆናል የሚለውን መፍታት የሚቻለው በብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ሲሆን፣ እንደ ሀገር ተቋቁመው ወደሥራ መግባታቸው የሚታወቅ ነው፤ እኛ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል እንደ መንግሥት ከእኛ የሚጠበቅንና



የሚያስፈልግ ነገር በተለይም በጉዳዩ የሚሳተፉ አካላትን መልምለን እንዲሳተፉ ማድረግ አንዱ ሒደት ነው። እንዲሁም አጀንዳ ሊሆኑ ይችላሉ የምንላቸውን ጉዳዮች በማቅረብ ላይም እንሠራለን፡።

ዋናው ድጋፍ ማድረግ እና የማያግባቡን ጉዳዮች ላይ ሰው በነቂስ ወጥቶ ተወያይቶና ተመካክሮ እንዲፈታው ድጋፍ ማድረግ ነው። እንደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከቀበሌ ጀምሮ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲሳተፉ ሊሠሩ የሚችሉ አካላት ጋር ውይይት ቢጀመር የሚለውን እየተነጋገርን እንገኛለ፡፡ በጥቅሉ በችግሮቻችን ላይ እና በልነቶቻችን ላይ ያሉ አለመግባባቶች ካሉ ተነጋግረን እንፈታለን የሚል እምነት ስላለን መልክ የሚይዝ ይመስለኛል። በመሆም በተቻለን ሁሉ ደግፈን ወደተግባር ፈጥኖ እንዲገባ የበኩላችንን እንደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከጥቂት ሳምንት በፊት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ለፓርላማ አባላት ስለ ቀይ ባሕር እና ስለ ባሕር በር ጉዳይ ገለጻ ማድረጋቸው ይታወሳል፤ በባሕር በር ጉዳይ አጀንዳ ላይ የእርስዎ አተያይ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጥላሁን፡-** ኢትዮጵያ እንደሚታወቀው በጣም ትልቅ ሀገር ናት፡፡ የምንገኝበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ላይም ድርሻዋ ጉልህ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በሕዝብ ብዛትም ደረጃችን ከፍ ያለ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ያለን የተፈጥሮ ሀብትም በተመሳሳይ ከፍተኛ በመሆኑ በጥቅሉ በአካባቢያችንም ሆነ በቀጣናችን ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን ሳይታለም የተፈታ ሐቅ ነው፡።

ነገር ግን ትልቅ ፈተና የሆነው ከዚህ ቀደም የባሕር በር ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ ሀገራችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደብ አልባ ሆናለች፡፡ ግን ደግሞ ለብዙ ሀገራት የተፈጥሮ ጸጋ የሆነውና በጣምም ውድ የሆነው ውሃ በወንዞቿ አማካይነት ስትገብር ትስተዋላለች። የእኛን ወንዝ የሚጠቀሙ በጣም በርካታ የአፍሪካ ሀገራት አሉ፤ እኛ ግን ከእነሱ የምንጠቀመው ነገር ብዙም የለም፡፡

የባሕር በር ቢኖረን የሚለው ጉዳይ አጀንዳ ሆኖ ለሕዝብ መቅረቡ እንደእኔ ጊዜውን ጠብቆ በትክክኛ ወቅት የመጣ እና እንዲሁም ኢትዮጵያ የራሷ የባሕር በር ኖሯት የውስጥ ልማቷንም ሆነ አጠቃላይ በቀጣናው በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ያላትን ተጽዕኖ ልታሳይ ይገባል ባይ ነኝ። በመሆኑም ጉዳዩ ዋና አጀንዳ ሆኖ በፍጥነት ከጫፍ ጫፍ መነጋገር፣ መወያየትና መግባባት የሚገባን ጉዳይ ነው ብዬ እወስዳለሁ። የባሕር በርና የወደብ ጉዳይ ጊዜውን ጠብቆ የመጣ ትክክለኛ አጀንዳ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ መንግሥት ጉዳዩን አጀንዳ አድርጎ ተነጋገሩበት መባሉ ትክክለኛ ነው የሚል አተያይ አለኝ።

መንግሥት አጀንዳ አድርጎ ሲያቀርብም የባሕር በርን በጉልበት እንውሰድ ማለቱ አይደለም። አጎራባች ከሆኑ ሀገራት ጋር በስምምነት፣ በውይይት በመነጋገር እና በመግባባት ለሁሉም ሕዝብ ጠቃሚ በሚሆን መልኩ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ሰው ጉዳዩን እያነሳ ከኤርትራ ጋር ሲያገናኘው ይስተዋላል። በተመሳሳይም ከሌሎች ሀገሮች ጋር ያገናኘዋል። ዋናው ሁለቱ ሕዝቦች የባሕር በር ያላቸው ብዙ መጠቀም ወይም ደግሞ መገልገል ያልቻሉትን እኛ የጋራ አድርገን መገልገል ስላለብን የሁለት ሀገራት ሕዝቦች ተጠቃሚ መርህን ተከትለው በጋራ እንገልገል፤ አጀንዳ አድርገን እንወያይበት፤ የተለያዩ ስልቶችን ነድፈን ተግባቦት እየፈጠርን እንሂድበት የሚል አመለካከት አለኝ። ደግሞም አጀንዳ መሆኑ ማንን ይጎዳል፤ የባሕር በርም ደግሞ ያስፈልገናል። ስለዚህ አጀንዳ አድርገን ጀምረናል፤ በሒደት ደግሞ ተጠቃሚ ስንሆን አጀንዳው ይቋጫል፡፡ ይሁንና በአሁኑ ወቅት አጀንዳ ሆኖ ጥንስሱ እንዲጠነሰስ መደረጉ ተገቢም ወቅቱን የጠበቀም ነውና ትክክለኛም ውሳኔ ነው ብዬ እወስደዋለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አዲሱን የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በርዕሰመስተዳድርነት ለመምራት በተሰጥዎ ኃላፊነት ከሌሎች አመራር ጋር በመሆን ምን ዓይነት ደረጃ ላይ ለማድረስ አስበዋል? ክልሉ ባለሀብቶች መጥተው እንዲያለሙበት የሚያስችልስ ምን ምን ነገር አለ?**

**አቶ ጥላሁን፡-** በታሪክ አጋጣሚ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የመጀመሪያው ርዕሰመስተዳድር ሆኜ እንድመራ ድርጅትም መንግሥትም መርጦ ሕዝቡ ደግሞ ይሁንታውን ሰጥቶኝ በመሥራት ላይ እገኛለሁ፡፡ ፓርቲዬ ይህንን ክልል ምራ ብሎ ሲሰጠኝ እንደሚታወቀው ክልሉ በጣም ትልቅ ክልል ነው፡፡ በተፈጥሮም ጸጋ በጣም የበለጸገ ነው። ብዙ ያልለማ፤ ግን ደግሞ መልማት የሚችል ነው፡፡

ከእኔ ጋር በመሆን አብሮ ለመሥራት እና ሕዝብ ለመምራት የተቀመጥን አመራር አለን፡፡ በዚያ ልክ ደግሞ ክልሉን ለመቀየር በሙሉ ሞራል እና በሙሉ ኃላፊነት ወደ ተግባር ገብተናል፡፡ አደራ ወስደን መምራት ብቻ ሳይሆን ታሪካዊም አመራር ጭምር ነን ብዬ አስባለሁ፡። ይህን ጊዜ በተለይ አመራር ሆነን በምንመራበት ወቅት ትልቁ ግባችን እና ርዕያችን በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተው ክልል በኢኮኖሚም፣ በፖለቲካም የብልጽግና ተምሳሌት በመሆን ራሱን ችሎ ለሌላው የሚተርፍ እንዲሁም ደግሞ የእድገት እና የብልጽግና ተምሳሌት የሆነ ክልል እንዲሆን ነው።

**አመራር ሆነን በምንመራበት ወቅት ትልቁ ግባችን እና ርዕያችን በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተው ክልል በኢኮኖሚም፣ በፖለቲካም የብልጽግና ተምሳሌት በመሆን ራሱን ችሎ ለሌላው የሚተርፍ እንዲሁም ደግሞ የእድገት እና የብልጽግና ተምሳሌት የሆነ ክልል እንዲሆን ነው**

ዋና ግባችን የሠላም ተምሳሌ፣ የወንድማ ማችነት ተምሳሌት የሆነ ክልል እንፍጠር ነው። ስለዚህ ክልላችን በሠላም ተምሳሌትነት እንዲታወቅ እንሠራለን፤ ከዚህ ጎን ለጎን ክልላችን የፈተፈጥሮ ጸጋ ባለቤት ነው፡፡ ከደቡብ ኦሞ ዳሰነች ጫፍ እስከ ወላይታ ሶዶ አረካ ጫፍ ድረስ ያለው የተፈጥሮ ጸጋ ብዙ ያልተነካ እና ብዙ ያልተበላ ነው፡፡ ስለዚህ በትንሹ ከተረባረብንበት በጣም ከፍተኛ ውጤት ማምጣት የሚያስችል ጸጋ ያለው ነውና በሰው ኃይልም በተፈጥሮ ጸጋም በከርሰ ምድርም ይሁን በገጸ ምድር ሀብት የበለጸገ ክልል ነው፤ ይህንን አቅም እና ጸጋ በአግባቡ ለይተንና አውቀን በጊዜ የለንም መርህ ወደልማት ገብተን ከሠራን በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕዝባችንን ጥያቄ መመለስ እንችላለን፡፡

ይህንን ሁኔታ ተገንዝበን ወደሥራ መግባት በጣም ወሳኝ ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ ማስተላለፍ የምፈልገው በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በግብርናም ይሁን፣ በማኅበራዊም ይሁን በተለይ ደግሞ በቱሪዝም ኢትዮጵያ የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆን የበኩላችንን እንወጣ ነው፡፡ ደቡብ ላይ የቱሪስት መዳረሻዎች አሉ፡፡ ከዚህ ቀደም የለሙ እና በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሊለሙ የታቀዱ አሉ፡፡

በቱሪዝሙ ዘርፍ ሠላማችን የክልላችን አንዱ መገለጫ ነው። በግብርናም የተመቻቸ ሁኔታ አለ። የማዕድናት ሀብት ስላለን ባለሀብቶች ለራሳቸው ተጠቅመው ክልሉንም እንዲጠቅሙ ማድረግ መልካም ነው፡፡ ማንኛውም ኢንቨስት ለማድረግ ለሚመጣ አካል በራችን ሁልጊዜ ክፍት ነው፡፡ ሁኔታዎችን አመቻችተን ለማስተናገድ ዝግጁዎች ነን። ክልላችንም ሆነ ሀገራችን የበለጠ ሊያድግ የሚችለው ከግሉ ሴክተር ጋር ተነጋግረን ስንሠራ ነው፡፡

መላ ሕዝባችንም ደግሞ ከአመራሩ ጋር በምስረታ ጊዜ እኛን ደግፎ ሕዝበ ውሳኔውን እንዲሁም ደግሞ ምስረታ ወቅትም አለን በርቱ ብሎ ያሳየውን ድጋፍ አሁን ወደሥራ ስንገባም በተመሳሳይ መልኩ ድጋፉን እንዲቀጥል እንሻለን፡፡ ጥሪም እናቀርባለን። በተለይ ሠላሙን በማስጠበቁ በኩል፣ ልማቱንም በማሳለጡ ረገድ ከእኛ ጋር በመቀናጀት ይህንን ክልል የሠላም፣ የብልጽግ እና የወንድማማችነት ተምሳሌት እንዲሆን አግዙን እንላለን፡፡ አጋዥ የሆኑ የሚዲያ ባለሙያዎችም ሆኑ ሌሎችን አቅም በሚሰጥ አገዛችሁ ከእኛ አይለይ እላለሁ፡፡

በእስካሁኑ ሒደት ድክመቶቻችንንም ሆነ ጥንካሬዎቻችንን በግልጽ እየነገራችሁን እዚህ ደረጃ ደርሰናል፡፡ በቀጣይም ይህ እንዳይለየን እጠይቃለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን መረጃ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ጥላሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ - የክልሉ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች

አንተነህ ቸሬ

የተትረፈረፈ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት የሆነው የሲዳማ ክልል፣ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት በርካታ ምቹ ሁኔታዎችም አሉት፡፡ ክልሉ ያለው ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ሀገርን የሚያኮራ፣ ባለሀብቶችን በኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ የሚያነሳሳ እና የሕዝብን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መልካም አጋጣሚና ፀጋ ነው፡፡

የሲዳማ ክልል ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት የሀገር ኢኮኖሚ ዋልታ የሆኑ ምርቶች መገኛ ነው፡፡ በርካታ የክልሉ አካባቢዎች በቡና አብቃይነታቸው ይታወቃሉ፡፡ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶች የሚመረቱበት መሆኑም ይታወቃል፡፡ ዓይነተ ብዙ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች፣ የወተት፣ የዶሮ፣ የማር፣ የስጋና ሌሎች ሀብቶች በግብርናው ዘርፍ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ክልሉ ያለው የተፈጥሮ ሀብት ከግብርናው በተጨማሪ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ዕድል ይፈጥራል፡፡ የሲዳማ ክልል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በክልሉ ከ17 በላይ የማዕድን ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡ በአገልግሎት ዘርፍም ክልሉ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት አቅም አለው፡፡ የሲዳማ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው ሐዋሳ ከተማ ዙሪያ በርካታ የቱሪስት መስህቦች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክልሉ የሎካ አባያ ብሔራዊ ፓርክ፣ የበርካታ አዕዋፋትና እንስሳት እንዲሁም የተፈጥሮ ገፅታዎች እና የብዙ ባህላዊ የሽምግልና ስፍራዎች መገኛ በመሆኑ ለቱሪዝም ኢንቨስትመንትም ተመራጭ የመሆን አቅም አለው፡፡

ክልሉ በኢንቨስተሮች ተመራጭ እንዲሆን ከሚያስችሉት ነገሮች መካከል የእምቅ ሀብት ባለቤት መሆኑ፣ ሥራ ፈላጊ ወጣት የሰው ኃይል መኖሩ፣ ከአዲስ አበባ ናይሮቢ የሚዘልቀው መንገድ የክልሉን ዋና ከተማ ሐዋሳን አቋርጦ ማለፉ እና ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መኖር የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ክልሉን ከሀብቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ብዙ የኢንቨስትመንት ልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ በክልሉ የኢንዱስትሪ ክላስተር ዞኖችን በማደራጀት የክልሉን ሀብት ለኢንቨስተሮች የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል፡፡ የክልሉን የኢንቨስ ትመንት አቅምና ምቹ ሁኔታዎችን ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተሠሩ የንቅናቄ ተግባራት አማካኝነትም ብዙ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት እንዳላቸው ማወቅ ተችሏል፡፡ ክልሉ ትኩረት ከሰጣቸው የኢንቨስትመንት አቅጣጫዎች መካከል አንዱ በምርቶች ላይ እሴት (Value) ጨምሮ ለገበያ ማቅረብ ነው፡፡ ሲዳማ ክልል በቡና ሀብት ትልቅ አቅም ካላቸው የኢትዮጵያ አካባቢዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ለተከታታይ ዓመታት የጥራት ውድድር (Cup of Excellence) ላይ ቀርቦ አሸናፊ የሆነው የሲዳማ ቡና ነው፡፡

በክልሉ በ2015 በጀት ዓመት 99 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል፡፡ ባለሀብቶቹ ከሦስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ሲሆን፤ በኮንስትራክሽን (31)፣ በአገልግሎት (29)፣ በማምረቻ (22) እና በግብርና (17) ዘርፎች ይሰማራሉ፡፡ ፈቃድ ከወሰዱት ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ በክልሉ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ሲገቡ ለ17ሺ 800 ዜጎች (1896 ቋሚ እና ጊዜያዊ) የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡

**በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ለሚያስመዘግቡ 35 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ አምስት ቢሊዮን ብር ያስመዘገቡ 14 ፕሮጀክቶች (በኢንዱስትሪ ስድስት፣ በአገልግሎት ስድስት፣ በኮንስትራክሽን ሁለት) ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል**

በ2015 በጀት ዓመት አበረታች የኢንቨስትመንት አፈፃፀም ያስመዘገበው ክልሉ፣ በዘንድሮው የበጀት ዓመትም የኢንቨስትመንት ፍሰትን በማሳደግ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በዘርፈ ብዙ የማኅበረሰብ ተጠቃሚነት ዘርፎች የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ መታቀዱን በክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን፣ ፈቃድና መረጃ ዳይሬክተር አቶ ታሪኩ ሮባ ይገልጻሉ፡፡

ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፣ የክልሉን ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ሀብት በጥናት መለየት፣ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን የሚጨምሩ ጠንካራና ተከታታይ የፕሮሞሽን ሥራዎችን መሥራት እና ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተከታታይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ የበጀት ዓመቱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፉ አሠራሮችን አጠናክሮ ማስቀጠልም የእቅዱ አካል ናቸው፡፡

በ2016 በጀት ዓመት በክልሉ ለ12 የግብርና፣ ለ34 የኢንዱስትሪ፣ ለ20 የአገልግሎት እና ለ44 የኮንስትራክሽን ዘርፍ ፕሮጀክቶች፣ በአጠቃላይ ለ110 ባለሀብቶች፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዷል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶቹ በአጠቃላይ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል እንደሚያስመዘግቡም ተጠብቆ ነበር፡፡ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ለሚያስመዘግቡ 35 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ አምስት ቢሊዮን ብር ያስመዘገቡ 14 ፕሮጀክቶች (በኢንዱስትሪ ስድስት፣ በአገልግሎት ስድስት፣ በኮንስትራክሽን ሁለት) ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ ፈቃድ ከተሰጣቸው ፕሮጀክቶች መካከል በሴራሚክ ምርት ዘርፍ ለመሰማራት ፈቃድ የወሰደ አንድ ፕሮጀክት ከፍተኛ ካፒታል (አራት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር) በማስመዝገቡ በክልሉ በበጀት ዓመቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱ ፕሮጀክቶች ያስመዘግቡታል ተብሎ የታቀደውን የካፒታል መጠን በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ማሳካት ችሏል፡፡ በሩብ ዓመቱ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚወስዱ ፕሮጀክቶች ለ310 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ 888 ዜጎችን የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

አቶ ታሪኩ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለግብርና ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ አልተሰጠም ሲሉ ይጠቁማሉ፡፡ «አዲስ ፈቃድ ከመስጠት በፊት የቀድሞዎቹን የአፈፃፀም ደረጃ መገምገም አስፈላጊ በመሆኑ በዘርፉ ፈቃድ የወሰዱ ፕሮጀክቶች ኦዲት እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡» ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በግብርና ዘርፍ በገቡት ውል መሠረት ሥራ ያልጀመሩና አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ፕሮጀክቶችን የመለየት ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ባለሀብቶቹ በገቡት ውል መሠረት መፈፀም አለመቻላቸው በሩብ ዓመቱ በግብርናው ዘርፍ አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዳይሰጥ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰው፣ ባለሀብቶች ከሚያነሷቸው ችግሮች መካከል የብድር አቅርቦትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ዋናዎቹ ናቸው ይላሉ፡፡

የግብርና ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ኦዲት ከማድረግ ባሻገር፣ አብዛኞቹ የክልሉ አካባቢዎች አትክልትና ፍራፍሬ አብቃዮች በመሆናቸው በእነዚህ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶችም ልዩ ትኩረት ይሰጣል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ለክልሉ ኢንቨስትመንት፣ በተለይም ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች፣ እድገት ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ ዕድሎችና ግብዓቶች መካከል አንዱ ከሐዋሳ ከተማ በ45 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው ከታመነባቸው እና የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው በ2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሥራ መጀመሩ ይታወሳል፡፡

በአሁኑ ወቅት ከክልሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር ውል የፈፀሙ ኩባንያዎች በአቮካዶ፣ በማንጎ፣ በእንጆሪ፣ በቡና፣ በማር፣ በወተት፣ በስጋ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በአኩሪ አተርና በሌሎች ምርቶች ማቀነባበር ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል፡፡ በሙሉ አቅማቸው እየሠሩ ከሚገኙት ኩባንያዎች፤ የአቮካዶ ዘይት በማቀነባበር ለውጭ ገበያ፣ ወተት እና የተለያዩ የፍራፍሬ ጭማቂዎችን በማቀነባበር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲሁም የማር ምርትን ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡት አምራቾች ናቸው፡፡ ምርቶቹን ለሀገር ውስጥ ገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ ወደ ውጭ ለመላክ በተደረገ ጥረት አበረታች ውጤት ተገኝቷል።

አቶ ታሪኩ እንደሚሉት፣ የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ለምርት የሚያገለግለውን የጥሬ ዕቃ አቅርቦቱን የሚያገኘው ከአካባቢው ማኅበረሰብ ነው፡፡ የአካባቢው አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ አርሶ አደሮቹ የፓርኩ መጋቢ በሆኑ ሦስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት (በንሳ ዳዬ፣ አለታ ወንዶ እና ሞሮቾ አካባቢዎች የሚገኙ) እና በኅብረት ሥራ ማኅበራት በኩል የአቮካዶ፣ የማር፣ የወተት፣ የቡናና ሌሎች የግብርና ምርቶችን በፓርኩ ውስጥ ለተሰማሩ ለአልሚዎች እያቀረቡ ነው፡፡

የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የማር እንዲሁም የወተት ምርት የሚያቀርቡ ማኅበራት ግብዓቶችን የሚሰበስቡት በገጠር የሽግግር ማዕከላቱ በኩል ነው፡፡ ፓርኩ ግብአቶችን በማቅረብ የገበያ ትስስርና የገቢ ምንጭ ከፈጠረላቸው አርሶ አደሮች በተጨማሪ በየአመቱ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ይህ ተግባር የሥራ ዕድል የመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪ ወጪን የማስቀረትና ገቢ ምርቶችን የመተካት ድርብርብ ዓላማዎች አሉት፡፡ ከሦስት ዓመታት በፊት ትልቅ ገበያ ያልነበረው የአቮካዶ ምርት በአሁኑ ወቅት ደረጃ ወጥቶለት አርሶ አደሩ ምርት በስፋት እያቀረበ፣ ገቢ እያገኘና አዳዲስ ዝርያዎችን እያለማ ነው፡፡ ፓርኩ አርሶ አደሩ ጥሬ ዕቃን በብዛትና በጥራት እንዲያቀርብ ዕድል እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ይህም የግብርና ምርታማነት እንዲጨምርና የአርሶ አደሩ ሕይወት እንዲሻሻል እያደረገ ነው፡፡

«በፓርኩ ውስጥ የተሰማሩ ባለሀብቶች ግብዓቶችን ከየአካባቢው ሲሰበስቡ ለአርሶ አድሮች ሥልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች ግብዓቶች በጥራት እንዲቀርቡና ምርታማነት እንዲጨምር እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ስለሆነም ፓርኩ የግብዓቶችን ጥራት በማሻሻል ምርታማነት እንዲጨምር ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። ሲሉ ጠቅሰው፣ ፓርኩ ለግብርና ኢንቨስትመንት እድገት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል» ብለዋል፡፡

«በፓርኩ ዙሪያ ያሉ አካባቢዎች ለፓርኩ ግብዓት የማቅረብ አቅም ያላቸው በመሆኑ በፓርኩ ውስጥ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ተግባራት ለአርሶ አደሮች የገበያ ትስስርም ሆነ የሥራ ዕድል በመፍጠር የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ ናቸው፡፡ ባለሀብቶች ወደ ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው እንዲያለሙ የሚከናወኑት የፕሮሞሽን፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የክትትል ተግባራት በልዩ ትኩረት ይከናወናሉ ሲሉ በመጠቀስ፣ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ለክልሉ የግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ መጠናከር ያለውን ሚና ያስረዳሉ፡፡

በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ስለሚከናወኑ ተግባራት በሐዋሳ ሐይቅ ዙሪያ ትልልቅ ሆቴሎችንና ሪዞርቶችን በመገንባት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንም ነው ያመለከቱት፡፡ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን በማከናወን የሐዋሳ ሐይቅን፣ የአላሙራ እና የታቦር ተራሮችን እንዲሁም ጉዱማሌ አደባባይን ለቱሪስቶች ምቹ የማድረግ ሥራዎችም ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡ የመስህብ ስፍራዎችን ለማልማት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶች የመሬት ዝግጅትና ሌሎች ግብዓቶች በፍጥነት እንዲሟሉላቸው እንደሚደረግም አመልክተው፣ ባለሀብቶች በቱሪዝም ዘርፍ በስፋት እንዲሰማሩ በ2016 የበጀት ዓመት የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራዎች እንደሚከናወኑ አስታውቀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በርካታ ወጣቶች በሐዋሳ ሐይቅ አካባቢ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡ በክልሉ በተለይም በሐዋሳ ዙሪያ የመዝናኛ ማዕከላትን መገንባት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉም ተናግረው፣ ብዙ ባለሀብቶች በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩና ጥያቄ እያቀረቡ እንደሆነም ይገልፃሉ፡፡

በክልሉ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክ ቶች የክልሉን ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ሲከናወኑ የነበሩ ተግባራት በዘንድሮው የበጀት ዓመትም ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አቶ ታሪኩ ይናገራሉ። «ከዚህ ቀደም ትምህርት ቤቶችን (አለታ ወንዶ) እና የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማትን (ሐዋሳ ዙሪያ) ገንብተው ያስረከቡና ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ባለሀብቶች አሉ። በቴክኖሎጂ ሽግግር ረገድ ደግሞ፣ አርሶ አደሮች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲላመዱ ያስቻሉ ቁሳቁስንና አሠራሮችን አበርክተዋል፡፡ በ2015 የበጀት ዓመት 480 የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። በዶሮ እርባታ እና በንብ ማነብ ዘርፎች የተከናወኑ ተግባራት ለዚህ አበርክቶ የሚጠቀሱ ማሳያዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ተግባራት አጠናክሮ ማስቀጠል የበጀት ዓመቱ የዘርፉ እቅድ አካል ነው» ይላሉ፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

## መልካም ንግግር ያድምቀን

ምሕረት ሞገስ

ክረምት ማለፉን ተከትሎ ደማቁ ፀሐይ ምድሪቷን እያሞቀ፤ የግሮሰሪውን ሥራም እያደመቀው ነው:: ከተገናኙ የከራረሙት ተሰማ መንግስቴ፣ ዘውዴ መታፈሪያ እና ገብረየስ ገብረማርያም ዛሬ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ደግ ደጉን መነጋገር ጀምረዋል። ተሰማ ፊቱ ሞላ ብሎ ወፍሯል:: ገብረየስም ፊቱ ላይ የነበረው ማድያት ጠፍቷል:: ዘውዴ ግን አልተመቸውም፤ ሰውነቱ ቀንሷል:: ድሮም ያልነበረች ቦርጭ አሁን ጭራሽ ጠፍታለች::

ገብረየስ ‹‹ትርጉም የማይሠጥ ትግል ከማበሳጨት አልፎ አንዳንዴ ፈገግ ያሰኛል:: በንግግርም ሆነ መሣሪያ በመምዘዝ የሚካሔድ ትግል መጨረሻው ሲታይ፤ እንደሰከረ ሰው በማያስደስት እና ሊያስለቅስ በሚገባ ጉዳይ ለመሳቅ ያስገድዳል:: ጊዜው በሆነ አጥር ውስጥ ገብቶ የሆነ ትግል ውስጥ ለመገኘት ደንዘዝ ማለትን ይጠይቃል:: መደንዘዝ ደግሞ ራስን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብን አልፎ ተርፎ ብዙ ሰዎችን እና ሀገርን ሊጎዳ ይችላል:: ስለዚህ ለእያንዳንዱ ነገር ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: በመልካም ንግግር መድመቅ ይሻላል:: በመልካም ንግግር መድመቅ ካልቻልን ቢያንስ ከንግግር ይልቅ ዝምታን የመረጥነው ለእዚሁ ነው:: ያምራል ብሎ ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው ይሻላል ይባል አይደል? የማይጠቅም ነገር ከመናገር መቆጠብ ይሻላል::›› አለ::

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ልፉ ያለው ግድግዳ ሲገፋ ያድራል እንዲሉ፤ ልፉ ያለን ግድግዳ ስንገፋ እንውላለን:: ከተገነባው ግድግዳ በላይ ግንብ ገንብተን ራሳችንን በከፍታ ላይ ማስቀመጥ ስንችል፤ ጊዜያችንን ግድግዳ በመግፋት እናባክናለን:: ቃል በማውጣት ብቻ ሳይሆን፤ መሣሪያ እየመዘዝን ተራራ እና ሸንተረሩን እየሮጥን ከላብ አልፈን ደም እናፈሳለን፤ ተኩሰን እየጣልን፤ ተተኩሶብን እየወደቅን እንሰዋለን::

የፈሰሰ ደም ላይመለስ አፈር ውስጥ እየሰረገ ሲደርቅ ዓይናችንን እያጭበረበረ ማንፀባረቁ ቢያውከንም፤ ክርፋቱ አፍንጫችንን ለመቁረጥ ጫፍ ቢደርስም፤ ‹ተጨቁነናል› በሚል፤ ጨቋኙ ማን እንደሆነ በደንብ በውል ሳንለይ፤ ተገቢውን ውጤት ላናገኝ ላባችንን እና ደማችንን ከማፍሰስ ወደ ኋላ ብለን አናውቅም::

በንግግር እና በመተባበር ሠላም ለማምጣት ከመጣር ይልቅ፤ ከፋፋይ በሆኑ ሃሳቦች ተጠምደን መደገፍ ያለብንን ሳይቀር እየተቃወምን ጊዜያችንን፣ ጉልበታችንን፣ ሀብታችንን እና ሙሉ ማንነታችንን እንቀብራለን:: የአዋቂ ሴት ቤት አለው ውበት ይባላል:: አዋቂ ሴት ቤቷን በሥነሥርዓት ይዛ ታሳምራለች:: እኛ ግን ቤቷን ያሳመረች ባለሞያ ሴትን ስናይ ከማድነቅ ይልቅ እንሳለቃለን:: የሠራችውን እናጣጥላለን፤ ለሠላም ከመረባረብ ይልቅ በምላሳችን መርዝ እንረጫለን:: ቤት ለማፍረስ የቻልነውን ሁሉ ጥረት እናደርጋለን።›› ሲል መረር ብሎ ተናገረ::

ዘውዴ እንደሌላ ቀን ለመከራከር አልሞከረም፤ ደክሞታል:: ሕልም በመሰለ ዓለም ውስጥ እንደሚኖር ሰው ዓይንኑን ቡዝዝ አድርጎ በውል ምን እያሰበ እንደሆነ ለመገመት በሚያስቸግር መልኩ ፈዝዞ ቀረ:: ሁለቱም ልብ አላሉትም::

ገብረየስ ቀጠለ፤ ‹‹በውል ማንነቱን ያልለየነውን ምናልባትም ጨቋኝ ያልሆነውን እናገኛለን ብለን፤ የማይፈርስ ግድግዳ ለመጣል በምናደርገው ትግል ዋጋ የሌለው መስዋትነት እንከፍላለን። አልገፋ ብሎ እንደግድግዳ ተገትሮ የጋረደንን ግንብ ስንገፋ እንደማይወድቅ መገንዘብ የተሳነን ከመሆናችን ባሻገር፤ ተሳክቶልን ቢወድቅ እንኳ፤ ከእርሱ መውደቅ ቀጥሎ ምን እንደምናደርግ ለይተን አናውቅም:: ጥለን እንደምንነሳ እና እንደምንደሰት እንዲሁም ከዚያ በኋላ ግድገዳ እንደማንገፋ እርግጠኞች አይደለንም::

በተደጋጋሚ ለመጣል ከመታገል አልፈን በመውደቁ ተጎጂ የምንሆንበት አጋጣሚ ሊፈጠር እንደሚችል አንገምትም:: በጭራሽ ስለራሳችን ጥሎ መነሳት እና በትግላችን ሒደትም ሊመጣብን የሚችለውን ጉዳት አናስብም:: የቀን እና የሌሊት ህልማችን እልሃችንን የምንወጣበትን ሁኔታ መፍጠር ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው::

ግንቡ መኖሩ ምናልባትም ተንሻፎ ከሚዘንብ የዝናብ ውሽንፍር የሚያድነን ይሆናል:: ነገር ግን አዕምሯችንን ለዚህ አላዘጋጀነውም:: ግንቡ ያለውን ጠቀሜታ ለመገንዘብ አንፈልግም። ተደጋጋሚ ሃሳባችን የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ እንደሚባለው ግንቡ ከክፉ ነገር ሳይሆን ከደግ ነገር ከልሎናል የሚል ብቻ ነው:: ከክፉም ከደጉም የከለለንን ግንብ አፍርሰነው ለመበስበስ እንሯሯጣለን::

የዘነበ ዝናብ አበስብሶ አጥንታችን እየተሰነጠቀ መሆኑ እየተሰማን በጥፋታችን ከመፀፀት ይልቅ፤ በራሳችን የጀመርነው የማያዋጣ ግድግዳ የመግፋት ተግባራችንን አጠናክረን እንቀጥላለን። የታገልነው የገፋነው ግንብ ቢወድቅ እንኳ፤ በእርሱ መውደቅ እኛ ካልወደቅን ደግሞ ሌላ የሚፈርስ ግድግዳ እንፈልጋለን:: መለስ ብለን አስበን የሚያዋጣንን ፈልገን፤ የማያዋጣንን ትተን ከመጓዝ እና የራሳችንን ወደ ከፍታ የሚያደርሰንን ግንብ እንገንባ የሚል ሃሳብ በፍፁም ብልጭ አይልልንም::›› ሲል ገብረየስ የውስጡን ተናገረ::

ተሰማ የገብረየስን ሃሳብ በመደገፍ እርሱም በበኩሉ፤ ‹‹ትክክል ብለሃል በተደጋጋሚ ሃሳባችን ገፍትሮ መጣል፤ ታግሎ ማፍረስ ላይ የተጠመደ ነው:: ለራሳችን የሚያዋጣንን መንገድ አስበን ለመለየት እንቸገራለን:: ግማሹ ምን ቢደረግለት ወይም ምን ቢያገኝ ትግሉን እንደሚያቆም እንኳ አያውቅም:: የኋላ ታሪክ ላይ ተቸንክረን እየታገልን ግፍ ተፈፀመብን እያልን ስንማረር፤ ያለፈ ድርጊት ለመበቀል የማይደረስበትን ሰማይ ለመቧጠጥ መጣጣርን እንደልማድ ቆጥረነዋል::

በተለይ ተበድለናል ብለን ስናስብ፤ እውነት ሆኖ የተፈፀመ ግፍ ቢኖር እና ተጨባጭ መረጃ ብናገኝ እንኳ፤ ስለተፈፀመው ግፍ በምን መንገድ ማን ካሳ መክፈል ወይም ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት በእርግጠኝነት ለይተን አናስቀምጥም። ጭራሽ ማን ተጠያቂ መሆን እንዳለበት ሳናውቅ የገዛ ቤታችንን ጓዳችንን እያመስን የጠላት መደሰቻ እንሆናለን::›› ሲል፤ ዘውዴ በበኩሉ ለካ በዝምታ ሲያዳምጣቸው ቆይቷል፤ እንደመባነን ብሎ እርሱም የሚያምንበትን መናገር ጀመረ::

‹‹ግራ የሚጋቡን ብዙ ነገሮች አሉ:: በዚያ ላይ ግራ የሚያጋባን ነገር ግልፅ እንዲሆን በግልፅ፣ በትህትና እና አንዱ ሌላውን ባከበረ መልኩ የተነጋገርንበት ሁኔታ የለም:: በእርግጥ ትግል ሁሉ መጥፎ አይደለም:: የነፃነት ትግል ሲካሔድ ባርነትን ምረጡ ከትግል ወደ ኋላ በሉ ማለት አይቻልም:: በኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ላለመገዛት የተካሔደው እልህ አስጨራሽ ትግል ተገቢ እና ትክክለኛ ነው::

ቅኝ ገዢ ግንብም ሆነ ተራራ በትግል ተገርስሷል:: የእዚህ ትግል መነሻ እና መድረሻ ማንኛውም ታጋይ በደንብ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: ከፋሽስት ጋር ታግለን ነፃነታችንን ማረጋገጣችን፤ ለጥቁር አፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ በቅኝ እየተገዙ ለነበሩ ሁሉ ብርሃን ማሳየታችንን የምትዘነጉት አይመስለኝም::›› በማለት የትግልን አስፈላጊነት ሲያብራራ ተሰማ አቋረጠው::

ተሰማ ፤‹‹የውጭ ጠላትን ለማባረር የሚደረግ ትግል ተገቢ እና ትክክለኛ ነው:: በሀገር ውስጥ ወንድም በወንድሙ ላይ እየተነሳ የሚካሔድ ትግል ግን ትርፍ ሲያስገኝ አላየንም:: አንዳንዱ ታጋይ ነኝ ባይ ‹ የምታገለው ቡድኔን፣ ጎሳዬን፣ ብሔሬን ነፃ ላወጣ ነው፤› ወይም ‹ይሔንን ነገር የእኔ ወይም የዚህ ቡድን፣ የዚህ ጎሳ፣ የእዚህ ብሔር ለማድረግ ነው::› ይላል:: ነገር ግን የትኛው ቡድን የየትኛውን ቡድን፣ ጎሳ ወይም ብሔር ነፃነት ገፈፈ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልስ ለማግኘት ማዳገቱ አይቀርም::

እንፋለምለታለን የሚባለው ነገር በፍፁም የአንድ ሰው የአንድ ቡድን ወይም የአንድ ብሔር መሆን የለበትም:: ምንም ሆነ ምን አንድ የጋራ የሁሉም መሆን ያለበትን ጉዳይ ምንም እንኳ አንዱ ተነስቶ የእኔ ቡድን፣ ጎሳ ወይም ብሔር መሆን አለበት ብሎ ወስኛለሁ ለማለት ቢሞክርም፤ በፍፁም ሊሆን የሚችል አይደለም:: ሌላውም ጉዳዩ የእኔ ነው ብሎ ብዙ መስዋትነት ቢከፍልም፤ የእርሱ ብቻ መሆን አይችልም:: ምክንያቱም ጉዳዩ የሁሉም ነው:: በተለይ በሕፃናት ጨዋታ ላይ እንደሚገለፀው ሀገራዊ ጉዳይ ከተነሳ ሀገር የጋራ ነው::

የኢትዮጵያ ውሃውም፣ ማዕድኑም፣ አፈሩም ሆነ አጠቃላይ ምድሩ የመላው ኢትዮጵያውያን ነው:: ይህ አሁንም ሆነ ወደ ፊት የሆነ እና መሆን ያለበት ጉዳይ ነው:: ታዲያ ይህ ከሆነ የትግላችን ሥሩ ዋነኛው ምክንያት በውል ሳይታወቅ፤ ግማሹ እኩሌ ስለታገለ እኔም እታገላለሁ ሲል፤ ገሚሱ ደግሞ ታሪክ ሆኖ ተመዝግቦ መታለፍ ያለበትን ጉዳይ የሙጥኝ ብሎ ሕይወቱን መስዋት ለማድረግ ሲሰናዳ እየተመለከትን አብረን ለትግል መነሳታችን በእርግጥም ከማሳዘን፣ ከማበሳጨት አልፎ ፈገግ ያሰኛል:: ትናንትን እያሰቡ ዛሬን ማበላሸት ባለማወቅ የሚሠራ ሥራ እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም:: ›› ሲል ሃሳቡን ደመደመ::

ገብረየስ ግን ሃሳቡን አልቋጨምና እምነቴ ያለውን ለመግለፅ ወደደ:: ‹‹መታወቅ ያለበት አንድ ሰው በወንድሙ ላይ ሲነሳ፤ መጨረሻው መጥፎ ነው:: ትግሉ አንዱ ሌላውን ለመጣል ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ለመጣል ሲታሰብ መውደቅ ያጋጥማል:: አንድ ወንድም ከወንድሙ ጋር ተነጋግሮ ችግሮችን መፍታት ሲቻል፤ ሰበብ እየፈለጉ እጅ እየጨበጡ በወንድም ላይ ቡጢ እየሰነዘሩ መታገል በተደጋጋሚ አይተነዋል፤ አድርገነዋል፤ ነገር ግን አዋጪነት የሌለው መሆኑን ከእኛ ውጪ ምስክር አይገኝም:: እየተጋጩ ከገዛ የእናት ልጅ ጋር እየተቦጫጨሩ፤ እየተላላጡ ከመቁሰል እና ኃይል ከመጨረስ ይልቅ፤ ዕድል ሲያጋጥም ልክ እንደማንኛውም ጓደኛ ተነጋግሮ ችግሮችን መፍታት ይሻላል::›› አለ::

ተሰማ ሃሳቡን ቢጨርስም የገብሬ ሃሳብ አነሳስቶት፤ ለመናገር ፈለገና ቀጠለ፤ ‹‹ምንም እንኳ አንዱ ከሌላው በሀብትም ሆነ በጉልበት በልጦ ማሸነፍ ቢችልም፤ የእናት ልጅን ማርኮ የትም መድረስ አይቻልም:: ይልቁኑ ያለው ይበቃናል ብሎ ተስማምቶ መኖር ይበጃል:: ተስማምቶ እና ተባብሮ በመኖር ማጣት ሳይሆን ማግኘት ያይላል:: ግድግዳ ለመግፋት የሚውለውም ኃይል ሥራ ላይ ውሎ ሀገር ይቀየራል:: ነፃነት ገፋፊ ባልተለየበት መልኩ መታገልም ሆነ፤ የመላ ቤተሰቡን ሀብት ‹‹የኔ ነው፤ ያንተ ነው›› ብሎ እየተስገበገቡ መናቆር ውጤት አያመጣም። በተቃራኒው ካልተገባ ትግል ይልቅ የቤተሰብን ሀብት የበለጠ ለማሳደግ አቅዶ መሥራት እና ጉልበትን ሕዝብን በሚጠቅሙ ሁኔታዎች ላይ ማዋል የተሻለ ነው::

በእርግጥም እኔም እንደማምነው የተበላሸውን ማስተካከል ቀላል አይሆንም:: ተደጋጋሚ ትግል ያስፈልጋል:: የጠገበን ማረቅ የግድ ነው:: በደም ፍላት ሳይሆን በብልሃት መሥራት ይገባል::›› አለ።


ገብረየስ የሕይወት ተሞክሮውን በማንሳት ጓደኞቹን ለመምከር አሰበ:: ‹‹ምንጊዜም ቢሆን ሁለታችሁም መጠንቀቅ አለባችሁ:: ከላይም ሆነ ከታች በደም ፍላት የሚንቀሳቀሱትን መደገፍ የለባችሁም:: ሳያስቡት በደም ፍላት የሚፋለሙ ብዙ ጊዜ መጨረሻ ላይ አይሳካላቸውም:: ጊዜያዊ ድል ቢያስመዘግቡም ድሉ እና ደስታቸው ከእጃቸው መውጣቱ አይቀርም:: ምክንያቱም በደም ፍላት የሚፈፀሙ ድርጊቶች የሚመጣውን ጣጣ ግምት ውስጥ የማያስገቡ በመሆናቸው፤ በአብዛኛው ጎጂ ናቸው:: በሕይወታችሁ ግጭት እና ጦርነትን ከማሰብ ይልቅ መልካሙን ነገር ደጋግማችሁ አስቡ:: በጎ በጎውን ተናገሩ:: ማር ሲሰፍሩ ማር ይናገሩ እንደሚባለው ማር ማር የሚል ነገርን ለመሥራት ሞክሩ:: አንድ አስደሳች ሥራ ሲሠራ ሥራው እንዲሳካ እና ትልቅ ውጤት እንዲገኝ ከሕዝብ የሚጠበቀው ጥሩ መናገር ነው። ጥሩ ሲናገሩ ጥሩ ሲሠሩ ጥሩ ውጤት ይገኛል::

ስለሠላም እና ስለሀገራችን እድገት እንሥራ፤ እናውራ:: ስለጦርነት መሥራት እና ማውራት እናቁም:: ስለበጎ ነገር ማሰብ፣ ስለበጎ ነገር መድከም እና መሥራት መልካም ነገርን ያመጣል። ለመልካም ነገር የሚተጉ፤ ከአፋቸው መልካም ቃልን የሚያወጡ ብዙ ባይጠቀሙም፤ አይጎዱም። መልካም ሠሪ እና መልካም ተናጋሪ እንዲሁም መልካም አድራጊ ሲበዛ ሀገራችን ታድጋለችና በበጎ ነገር እንተባበር::›› ሲል የዕለቱን ሃሳቡን ቋጨ እና የጠጡበትን ለመክፈል ኪሱን መዳበስ ጀመረ::

**ማር ሲሰፍሩ ማር ይናገሩ እንደሚባለው ማር ማር የሚል ነገርን ለመሥራት ሞክሩ። አንድ አስደሳች ሥራ ሲሠራ ሥራው እንዲሳካ እና ትልቅ ውጤት እንዲገኝ ከሕዝብ የሚጠበቀው ጥሩ መናገር ነው። ጥሩ ሲናገሩ ጥሩ ሲሠሩ ጥሩ ውጤት ይገኛል**

# የዘመን ጥበብ

# አባት አልባ ሕልሞች



**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አባት አልባ ሕልሞች...ከእውነተኛው የሕይወት ተራራ ስር ፈልቆ ግዙፍ ጅረት ለመሆን በቅቷል። ጥቅምት 18 ቀን 2016 ዓ.ም በርካቶች ወደዚሁ ተጠርተው ከተራራው ስር ከፈለቀው ንጹህ ጅረት በመጎንጨት ጥማቸውን አርከተዋል። እኛም ከጥሑሙ የጥበብ በረከት ተካፋይ ሆነናልና ካየነው፣ ከሰማነውና አንብበን ከተረዳነው ጥቂቱን እናቋድሳችሁ።

'አባት አልባ ሕልሞች' የብዙዎቻችንን ያልተፈታ ሕልም...ያልተከተበ ሕይወት...እንዲሁም ያልተኖረ ልጅነትን ያዘለ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ደራሲ ደግሞ ጋዜጠኛና ደራሲ ማስረሻ ማሞ ነው። በባዕድ ሀገር በኔዘርላንድስ ምድር ለ14 ዓመታት ያህል ቆይቶ ሲመለስ እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ አባት አልባ ሕልሞችን ከነቃጭሉ ይዞት መጣ። እዚሁ ታትሞ ተወለደና ኑ..ልጄን ስማችሁ መርቁልኝ በማለት ድግሱን በ'ስቴይ ኢዚይ' ሆቴል አሰናድቶ በዚሁ ባሳለፍነው ሳምንት ጥቅምት 18 ቀን ጠርቶ ነበር። እንዲህ ካለው ድግስ አይቀርምና በርካታ የጥበብ ቤተሰቦችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተው መጽሐፉን መርቀዋል። በእለቱ መጽሐፉ ብቻ ሳይሆን እጅግ ያማሩና የተዋቡ ባሕሎቻችን ክብረ በዓላቸው የነበረ ያህል በመድረኩ ገነው ታይተዋል። በመድረኩ ድባብ ከመንሰራፋታቸውም ባሻገር ተዳፍነው የቀሩ ባሕላዊ ትውፊቶችም በትርኢት ታጅበው ከነሙሉ ማንነታቸው ወደመድረክ የወጡበት አጋጣሚ ነበር።

ለመሆኑ 'አባት አልባ ሕልሞች' እንዴት ተወለደ? ማስረሻስ ይህን ታሪክ ለመጻፍ ልቡን የነሸጠው ጉዳይ ምን ይሆን?...እራሱ ማስረሻ በመድረኩ ላይ እንዲህ ሲል ባንደበቱ ገልጾታል፤ "ታሪኩ በሕይወቴ ሁሉ አብሮኝ የነበረ ቢሆንም የመጽሐፉ ጽንሰ ሀሳብ የተወለደው ግን በድንገተኛው የኮሮና ጎርፍ ነው። ከዚያም ኋላ በልቦለድ መልክ ልጻፈው ወይንስ እንደወረደ በሚል የሙግት ሜንጦ በስጋም በነፍስም ተሰቅያለሁ። በመጨረሻም ጥቂት የእውነት ጭብጦ ይገኜ በብዙ አሻሮ የሚሸሞነሞን አሻሮ ከምጽፍ ብዙ አሻሮ እውነታዎችን ጽፌ ነብሴን ባሳርፋት ይሻላል ብዬ የግል ታሪክ ተረኬን ለልጆቼ ለማውረስ ቆጥሜ ተነሳሁ። መጽሐፌን ለመጻፍ ከመጀመሬ በፊት እራሴን የጠየኩት አንድ ጥያቄ ነበር፤ እንደ ሰው ልጅ መኖር ከጀመርኩ ወዲህ የመጀመሪያው ትውስታዬ የተመዘገበው መቼ ነበር? የሚል ነበር። የሰው ልጅስ ከትውስታ ውጪ ምንድ ነው? በዚህ ጥያቄ አማካይነት 45 ዓመታትን ወደኋላ ተጉዤ እራሴን ማሰስ ጀመርኩ። እራሴን ስፈልግ እናቴን አገኘኋት። የእናቴን ዱካ ተከትዬ ስዞርም የመጽሐፉን ሕብለ ሰረሰር ጨበጥኩት፤ ሕብለ ሰረሰሩም እናቴ ነበረች" ሲል በመጽሐፉ ውስጥ የታሪኩ ሁሉ ምንጭ መነሻና እምብርት ከሆነችው ወላጅ እናቱን ጋር አጣቅሶ ይገልጸዋል።

ደራሲው ማስረሻ ማሞ ለዚህ መጽሐፍ መወለድ ዋነኛ ምክንያት የሆነችውን እናቱን በዚህ ልክ ሲገልጻት ዘጠኝ ወር በሆዷ ተሸክማ በሰቆቃ ወልዳ በሰቆቃ ከማሳደጓም ባሻገር፤ እናት በግሏም ከልጅነት ሕይወቷ ጀምሮ በሴትነቷ ስትፈተን፤ በባይተዋርነቷ የመከራን ጎርፍ ስትጋት ስለመኖሯ ተናግሯል። "እናቴ በሕይወት ድንገቴ ጎርፍ ውስጥ በአንድ ዓመት ከ6 ወሯ እናቷን አጣች። በ3 ዓመቷ ደግሞ አባቷ ጥሏት ጠፋ። በ5 ዓመቷ ድጋሚ አያቷን በሞት ተነጠቀች። ከዚያ በኋላም በአደራ የተቀበሏት አሳዳጊ ዘመዶቿ አሳልፈው ለአገልጋይነት ሰጧት። ይህ ስቃይ አያብቃልሽ ሲላት አግብታ ልጅ የወለደችላቸው ባሎቿ አንዳችም እገዛ አያደርጉላትም ነበር። እናት አልባ...አባት አልባ...ዘመድ አልባ...ሰማይ ቁልቁል የተደፋባትና ምድር የተከነበለባት በሰቆቃ የተከበበች ምስኪን ነብስ ነበረች" በማለት የአሳዛኝ እናቱን ሆድ የሚያስብስ የሕይወት ቋጠሮ በታፈነ ውስጣዊ ስሜት ይተርከዋል። በመጽሐፉ ውስጥ ያሰፈራቸው አሳዛኝ የሕይወት ጠብታዎች በእናቱ የተቋጩ አልነበሩም። 'ድንገቴ ጎርፍ' ሲል የሚገልጸው የሕይወት ማዕበል ከእናቱ አስጨከነች አልፎ የእርሱንም ሕይወት በሰቆቃ አጥለቅልቆታል። ስለልጆቿ የምትታገለዋን እናት የአቅም ድንበሯን ጥሶ እንደወረደ ለማስረሻም ተላልፏል።

እናትነት ለዋጋዋ ልኬት የለውም። ለውለታዋም ምላሽ አይገኝም። የአብዛኛዎቹ የቀጨኔ ልጆች የእውቀት በር የተከፈተው በአዳምና ሔዋን የቄስ ትምህርት ቤት ነው። ማስረሻም እንደ እኩዮቹ ገና በለጋነቱ ወደዚሁ የቄስ ትምህርት ቤት በመግባት እውቀትን ከፊደላት ገበታ እንዲቀስም እናቱ የነበራት ጉጉትና የከፈለችው መስዋዕትነት ከቃላት በላይ ነበር። ልጇ ተምሮ ሰው ይሆንላት ዘንድ ከወገቧ ላይ ከጠመጠመችው መቀነቷ ሀምሣ ሀምሣ ሳንቲም ትመድብለት ነበር። ይህን ተመልክቶ የእምባ ሲቃ የተናነቀው ማስረሻም ከመጽሐፉ ውስጥ ከአንደኛው ገጽ ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፤ "የእናቴን የመቀነቷን ጫፍ በተመለከትኩት ቁጥር የቤተሰባችን የሕይወት ሚስጥር እዚያ ውስጥ የተተበተበ መሆኑን አያለሁ...የሕይወታችን የሚስጥር ቋጠሮ የሚገኘው ከእናቶቻችን መቀነት ውስጥ ነው" አዎን እርግጥ ነው ማስረሻ እንዳለው ዛሬ የደረስንበትን የኛን ማንነት ያለ እናቶቻችን መቀነት ማሰቡ የማይሆን ነው። ትናንት የእነርሱን አንጀት በመቀነታቸው አስረው የኛን የዛሬ ሕይወት ፈተውበታል።

ከዚህች መጽሐፍ በስተጀርባ ያለው ግለታሪካዊ ልቦለድ ብቻ አይደለም። ከልቦለዳዊ የሰመመን ምጥቀትና ቋት ላይ ተመዞ ብቻም የተጻፈ አይደለም። ደራሲው ቀደም ሲል በንግግሩ እንዳመለከተው፤ የነበረውን ብዙ እውነት በፈጠራ ሳያሸሞነሙነው እንደወረደ አጣፍጦ አስፍሮታል። በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀማቸው ስሞችና መቼቶች እንኳን አንዳችም ለወጥ ሳያደርጉ እንደነበሩት አስቀምጧቸዋል። እናቱ አስጨከነች...ተራኪው ማስረሻ...ሁሉም በገሀዱ ዓለም መታወቂያቸው የቆሙ ናቸው። ዋናው ገጸ ባህሪ የሆነው ተራኪው ማስረሻ እራሱ ደራሲው ማስረሻ ማሞ ነው። በሕይወት ውጣ ወረድ ውስጥ አልፎ ለዛሬ የበቃባትን አሳዛኝ የታሪክ ሰበዝ ከምስኪኗ የቀጨኔ መንደር በመምዘዝ እውነታውን በብዕሩ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል። ብዙ አባት አልባ ሕልሞች ነበሩት፤ ነበረን። የራሱን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የብዙዎቻችንን እውነተኛ የኑሮ ሕቅታ አንዳችም ሳይደነቃቀፉ እኛነታችንን ይገልጻሉ። ማንነትና ባሕላችንን እስከዛሬ ባላየንበት አዲስ መነጽር እንድንመለከተው ያደርገናል። ማሕበራዊና ፖለቲካዊ እኛነታችንን አጉልቶና አቅርቦ ያሳየናል።

በመጽሐፍ ምረቃው ወቅት መድረኩን ሲያጋፍር የነበረውና የማስረሻ አብሮ አደግ ጓደኛ የሆነው ከፈለኝ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር። "የደራሲው ወንድሜ የቀጨኔ ሕይወት ልክ እንደ ቀጭኔ ነበር። ቀጭኔ ልጇን የምትወልደው በቁም ነው። የቀጭኔን ቁመት ተመልክቶ ልጇን ስትወልደው ያን ከሚያህል ከፍታ ላይ ወደ መሬት ስትፈጠፍጠው ማሰብ ለአዕምሮ ይከብዳል። የልጇ ስቃይ በዚህ አያበቃም፤ ተወልዶ መሬት ላይ ከወደቀበት ቅጽበት አንስቶ፤ እናት በዚያ ከባድ ሸኮናዋ ያላትን ኃይል በሙሉ ተጠቅማ እየደጋገመች ልጇን ትረግጠዋለች። ይህን ሁሉ የእናትነት አንጀቷ የወለደው ጥበብ እንጂ በጭካኔ አሊያም የልጇ ስቃይ ሳይሰማት ቀርቶ አይደለም። ምክንያቷ በዙሪያዋ ሆነው ልጇን ለሙብላት ካሰፈሰፉት አውሬዎች ለመታደግ ነው። እንዲህ የምታደርገውም ከዱላዋ ለማምለጥ በሚያደርገው መፍጨርጨር ቆሞ መሄድና ማምለጥ እንዲችል ነው። በአራት እግሩ ቆሞ መሮጥና ማምለጥ መቻሉን ስታረጋግጥ አሁን ብቁ ሆኗል በማለት መርገጧንም ታቆማለች። ለመጽሐፍ የበቃው የቀጨኔው ማስረሻ ሕይወትም እንዲሁ በቀጭኔ የተመሰለ ነበር"፡፡

በዚህ ታላቅ መድረክ ላይ ከተገኙ የጥበብ ሰዎች መካከል አንደኛው ተፈሪ ዓለሙ ነበር። መገኘት ብቻም ሳይሆን አጣፍጦ ለማቅረብ በተሰጠው ድንቅ ችሎታው ወደ መድረኩ በመውጣት ከመጽሐፉ ውስጥ ጥቂት ገጾችን ባማረ የትረካ ዘዬው ተርኮታል። ተርኮም ብቻ አልወረደም ስለ መጽሐፉ መሳጭ ታሪክና የደራሲው ችሎታ አድናቆቱን ከመግለጽ አልተቆጠበም። ከእርሱም ሌላ የቋንቋና ስነ ጽሁፍ ሊህቃን ከብዙ ነገሮች አኳያ በመገምገም አስተያየታቸውን ሰጥተውበታል። ከመጽሐፉ ዘውግ በመነሳትም አንድ መጽሐፍ ሊያካትታቸው የሚገባውን ዘውጎች ከመያዙም በላይ፤ በምርመራ ሂደት ቢያልፍ ምናልባትም ሁሉንም የዘውግ አይነቶች ልናገኝበት የምንችልበት ድንቅ ሥራ ነው ሲሉ አሞካሽተውታል። 14 ዓመታትን ከባሕር ማዶ ያሳለፈውን ማስረሻን በአባት አልባ ሕልሞች ውስጥ በተከማቸው የቃላትና የቋንቋ ችሎታ አጮልቀን ለማየት ስንሞክር ምናልባትም እራሳችንን እንታዘብ ይሆናል። እንደ ምናባዊ ትውስታዎቹ ሁሉ ቃላቱም ከጊዜው ጋር አብረው በያኔው የማወቅ ልኬት የተገለጡለት ይመስላል።

'አባት አልባ ሕልሞች' የአንድ ማስረሻ ግለታሪክ ብቻ አይደለም። እራሱ ደራሲው በመጽሐፉ ውስጥ ያስቀመጠውን የእርሱን የሕይወት መልክ ከሀገራችንና ከሕዝባችን ጋር አቆራኝቶ ብዙ እውነታዎችን ይነግረናል። የመጽሐፉ የጀርባ አጥንት የተገነባውም በሀገራዊ የፖለቲካና ማሕበራዊ ትስስር ውስጥ ነው። በአንድ ሰው ውስጣዊ መልክና ቁመና ውስጥ ቤተሰብ፣ ሀገርና ማሕበረሰብ አለ። "በዚህ ሁሉ ውስጥ አጨንቁሬ ኢትዮጵያን ለመመልከት ሞከርኩ። ኢትዮጵያ ግን ማናት? ለዚህ ሁሉ የዳረጋትስ ማነው? ብዬ ጣቴን ወደ መንግሥት ልጠቁም ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ። የአንድ ሀገር መሠረቱ ቤተሰብ ነው። እንደ ቤተሰብ የቤት ሥራችንን ያልጨረስን በመሆኑ እንዲህ አይነቷን ሀገር ፈጥረናል" ይላል ማስረሻ በቁጭት ውስጡን እየሸነቆጠው። ከመጽሐፉ ጭብጦች መካከል አንደኛው በዚሁ የሀገርና የቤተሰብ ሥርዓት ውስጥ ይዘዋወራል። የኢትዮጵያ ቤተሰብ በሁለት ነገሮች ተሠንጎ ስለመያዙ ያወጋናል። አንድም በውርስ ሁለትም በወሰን ተተብትቦ በአንድም ሆነ በሌላ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወታችንን አወሳስቦታል፡፡ አባት አልባ ሕልሞች ከእነዚህ ሁሉ እውነታዎች ጋር በመጋፈጥ ያለንበትን አስቀያሚ ሁኔታ እንድንለውጥ መንገዱን ያሳየናል። ስግብግቡ የሺጥላ፣ ራሷን ችላ መቆም ያልቻለችው ፋንቱ፣ ምስኪኗ የማስረሻ እናት... የመጽሐፉ የእውነት ፍልቃቂ ገጸ ባህሪያትና ማሳያዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ የቤተሰቡ አውራ የነበሩት የእትየ ጣፈጥን ሞት ተከትሎ እነዚህ ሰዎች በውርስ ምክንያት ተፋጠዋል፡፡ እነርሱን ለመዳኘት በሸንጎ የዳኝነት ሥርዓት የተሰየሙት ዳኞች የፍትህ አሰጣጥ በእጅጉ የሚያኮራና ወደኋላ ዞረን ያሉንን እንቁ ባሕሎቻችንን እንድንናፍቅ የሚያደርግ ነው። ደራሲው ተወልዶ ያደገበትን የባለ እጅ ማሕበረሰብ ባሕልና እሴት ከተደበቁበት ፈልፍሎ በማውጣት የመጽሐፉ ዋነኛ ግብዓት አድርጓቸዋል። በመጽሐፉ ውስጥ ከማንጸባረቁም በተጨማሪ በምርቃቱ መድረክ ላይ ምንም ሳይቀባባ ለታዳሚው በቀጨኔ እናቶች የቀረበው 'የእንጀራ ቆረሳ' የሚባለው የሴቶች የሽምግልና ሥነ ሥርዓት እጅን በአፍ የሚያስጭን ትዕይንት ነበር። ሴቶቹ "ልጃችሁን ለልጃችን" በማለት የትጭጭት ሥነ ሥርዓቱን የሚከውኑት በወንድ የተለመደውን ባሕላችንን በማፍረስ አይደለም። ይልቁንስ ነገሩ 'ሴት ያውቅ በወንድ ያልቅ' አይነት ነው። ሴት አምጣና ተጨንቃ የወለደች በመሆኗ ከወንዶቹ በፊት የልጆቻቸውን የትዳር መንገድ አስቀድመው በማጥራት የሚያስኬድ ከሆነ ጉዳዩን ወደ ቀጣዩና ወደ ዋነኛው የወንዶች ሽምግልና ያስተላልፉታል። ይህ የሴቶች እኩልነት፤ የእናትነት ክብር ነው። ዛሬ ላይ 'ሌዲስ ፈርስት' በማለት ነጮቹ የሚመጻደቁበት ሥርዓት ቀድሞ እኛ ጋር በባለ እጅ ማሕበረሰብ ዘንድ ነበር።

ሌላው የዚህ መጽሐፍ ምረቃ ከብዙ የመጽሐፍት ምረቃዎች ለየት ያደረገው አንድ ነገር ቢኖር በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱና በሕይወት ያሉ ሰዎችም በመድረኩ መገኘታቸው ነው። ከእነዚህም አንዷ ያቺ ምስኪኗ የማስረሻ እናት ነበረች። ...ለመሆኑ ክፍልፍልን የምናውቅ ስንቶቻችን እንሆን? "ክፍልፍል የስም ክህደት ተፈጽሞበታል" ይላል ማስረሻ በመጽሐፉ። እርግጥ ነው እንዲያ ቢል ውሸት አይሆንም። ዛሬ በብጣሽ እንጀራ አፈርፍረን የምራቅ ጠብታ በምታህል ዘይትና በርበሬ እንደነገሩ ለውሰን የምንውጣት ፍርፍር፤ የቀድሞ መጠሪያዋ ክፍልፍል ነበር። ለነገሩ ስሟን ብቻ ሳይሆን ማንነቷንም ቀይረነዋል። ድሮ ድሮማ ቋንጣና በእንጀራ ድርቆሽ እንዲሁም በቅቤ ተለውሳና ተከሽና ነበር የምትወጣው። ክፍልፍል ዘመናትን ተሻግራ አለሁ ስትል ከባለ እጆች ዘንድ ከነጉርሻዋ ለመድረክ በቅታ ነበር። ስትቀርብም ወዘናዋን እንዳጣችው እንደዛሬይቱ ፍርፍር በሳህንና በትሪ ሳይሆን በባሕሉ መሠረት በጣባ መሳይ ውብ ሸክላ ነበር የቀረበችው። ዋንጫ መሳይ የሸክላ መጠጫዎቹም ከነቅርጻቸው፤ ቀደምት ባሕላዊ ቅርሶቻችንን ያለ እውቅና መዘረፋችንን የሚናገሩ ነበሩ። ምስጋና ለአባት አልባ ሕልሞች ይግባና ከመጽሐፉም ሆነ ከምረቃው በስተጀርባ ብዙ እሴቶቻችንን ገልጦ አሳይቶናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ውብ ባሕሎቻችን ታጅቦ የዋለው የእለቱ የመጽሐፍ ምረቃ ሥነ ሥርዓት እንዲህ ባለ መልኩ ተጀምሮ... አለቀ፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ


## ትኩረት የሚሻው የብሬል መጽሐፍት ተደራሽነት

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ሞገስ ጌትነት ይባላል፡፡ በከፊል የእይታ ችግር አለበት፡፡ ከዓመታት በፊት ለዐይነ ሥውራን የሚሆን ሁለት የብሬል ቤተ መጽሐፍትን በየካቲት 12 እና በጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት አቋቁሟል። በዚህም ከዘጠነኛ ክፍል እስከ 12 ክፍል ያሉ አይነ ሥውራን ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተል፡፡ የሦስት ልጆች አባት የሆነው ሞገስ፤ በአሁን ወቅት የግል ሥራውን በመሥራት እንዲሁም ባለው ጊዜ የልጆች መጽሐፍ በመጻፍ የድርሰቱን ዓለም በሰፊው ለመቀላቀል መንገድ ላይ ይገኛል፡፡

በቅርቡም ‹ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች› የተሰኘ የልጆች መጽሐፍ ለንባብ አብቅቷል፡፡ ልጆች በስነ-ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ ለማድረግ፣ የአካባቢያቸውን እንዲሁም የአገራቸውን ታሪክ፣ ባሕል እና ቅርስ እንዲያውቁ ለማድረግ በምስል የታገዘ እና ልጆችን በሚመጥን መልኩ በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎ አዘጋጅቷል፡፡ መጽሐፉ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ስለመሆኗ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያን ያስተዋወቁ የታላላቅ ሠዎች ታሪክን አካቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች በዝርዝር ቀርበውበታል።

«የመጽሐፉ ዓላማ ልጆች አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ብሎም እንዲወዱ እና ከመደበኛ ትምህርታቸው ባሻገር ሌሎች መጽሐፍትን እንዲያነቡ ብሎም የንባብ ክህሎታቸው እንዲዳብር ለማድረግ ያለመ ነው፡፡» የሚለው ሞገስ፤ ስለብሬል ጠቀሜታ ቀድሞ ግንዛቤ ያለው በመሆኑ በተለይም ዐይነ ሥውራን ታዳጊዎች እንዲያነቡ ለማድረግ፣ በሥነ ጽሁፍ አማካኝነት ትምህርታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙ ለማስቻል ‹ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች› መጽሐፍን በብሬል ጭምር ለንባብ እንዲበቃ



**አቶ ሞገስ ጌትነት፣**

አድርጓል፡፡

የብሬል መጽሐፍት ውስንነቶች መኖራቸውን የተረዳው ሞገስ ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን መጽሐፉን በብሬል ጭምር ያዘጋጀው እንጂ ሥራው ፈታኝ መሆኑን ይናገራል፡፡ ወደ ብሬል ለመቀየር እንዲሁም የመጽሐፉ የሕትመት ዋጋ የሚፈትን መሆኑን በመጥቀስ፤ አጋዥ ካገኘ ግን ወደ ተለያዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በማምራት ለታዳጊ ዐይነ ሥውራን ተማሪዎች መጽሐፉን በስፋት ተደራሽ ለማድረግ እቅድ አለው፡፡

ሞገስ እንደሚገልጸው፤ ዐይነ ሥውራን ማንበብ ይፈልጉ እንጂ አብዛኞቹ የሕትመት ውጤቶች በብሬል የተዘጋጁ ባለመሆናቸው ይህንን እድል አያገኙም፡፡ ከንባብ ይልቅ በማዳመጥ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የወረቀት ዋጋ መናር እና ተያያዥ ችግሮች አንባቢ ትውልድ ለመፍጠር እንቅፋት መሆኑን በመገንዘብ፤ ችግሩን ያገናዘበ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

የብሬል ወረቀት ውድ መሆን፣ በይዘትም ሰፋ እና ገዘፍ ማለት እንደ አንድ ተግዳሮት የገለጸው አቶ ሞገስ፤ ቤተ መጽሐፍት ሲከፈቱ አካቶ ወይም ለአይነ ስውራን ተስማሚ የሆኑ ቤተ መጽሐፍትን መሥራት ቢቻል ችግሩን እንደሚያቀል ይመክራል። የተለያዩ ጸሐፊዎችም ድጋፍ ሊያደርጉላቸው የሚችሉ አካላትን በማፈላለግ እና ምሳሌ ሊሆን የሚችሉ ሥራዎችን በመሥራት የድርሻቸውን ቢወጡ፤ ዐይነ ሥውራን ያሻቸውን የስነ ጽሑፍ ውጤቶች እንዲያነቡ ያግዛቸዋል፡፡

«የሞገስ አንዱ ፍሬ ነኝ» በማለት ራሳቸውን የሚገልጹት አቶ ሆነልኝ መልኬ፤ የሞገስ ቀድሞ ተማሪና አሁን ደግሞ ጓደኛ ናቸው፡፡ በ1997 ዓ.ም አቶ ሞገስ «ዐይነ ሥውራን በትምህርት መታገዝ አለባቸው፡፡» ብለው ‹ኦሲስ የዐይነ ሥውራን ድጋፍ ማሕበር›ን በማቋቋም በትምህርት ላይ ብዙ ሥራዎችን መሥራታቸውን ያስታውሳሉ፡፡ በጥቁር አንበሳ እና በየካቲት 12 ትምህርት ቤቶች የዐይነ ሥውራን ቤተ መጽሐፍትን ማቋቋም በመቻላቸው፤ እርሳቸውም አንዱ ተጠቃሚ እንደነበሩም ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም በርካታ ዐይነ ሥውራን የሕይወት ክሕሎት ስልጠና እንዲያገኙ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

እንደ አቶ ሆነልኝ ገለጻ፤ የዐይነ ሥውራን ሕይወት በኢትዮጵያ አስከፊ የሚባል አይነት ነው፡፡ ችግሩ በትምህርት እና በሌሎች ላይም በስፋት የሚታይ ነው፡፡ ችግሩ በስፋት በሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ላይ የሚታይ ሲሆን፤ የድርሰት ውጤቶች ጉድለቶችን መሙላት አለባቸው፡፡ ነገር ግን በእኛ ሀገር ብዙ ጊዜ ደራሲያን ወይም የኪነ ጥበብ ሠዎች የሚዘነጉት የኅብረተሰብ ክፍል አለ። የተተወ (የተረሳ) ነገር ካለ በራሱ ሙሉ አይደለም ወይም ጎዶሎ ነው የሚሉት አቶ ሆነልኝ፤ መጽሐፉን በብሬል ማሳተም መቻል በራሱ ምልክት ነው በማለት ይገልጹታል፡፡

የሰባት ዓመት ታዳጊ እያሉ በዘመኑ በብሬል የታተሙ መጽሐፍትን አግኝተው ማንበብ አዳጋች እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ሆነልኝ፤ እንደ እነ ሞገስ ያሉ እና ዐይነ ሥውር ሕጻናት እና ታዳጊዎች እንዲያነቡ ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች መበረታታት እና መመስገን እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

ሞገስ በበኩሉ፤ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ እና ትብብር ማድረግ አለበት ይላል፡፡ «በእርግጥ በሥራ ቦታ ላይም ይሁን በትምህርት ቤት አካባቢ አጥጋቢ ባይሆንም የመንግሥት አስተዋጽኦ አለ ማለት ይቻላል» የሚለው ሞገስ፣ መጽሐፍትን ወደ ብሬል በማስቀየር እንዲሁም የብሬል መርጃ መሳሪያዎችን ድጋፍ የማድረግ ጥረቶች እንዳሉ ያስረዳል፡፡ ዐይነ ሥውራን ሠራተኞች በመንግስት ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ረዳቶችን በመቅጠር እንዲሠሩ እየተደረገ ያለው ጥረት መበረታታ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ «ለዐይነ ሥውራንም ሆነ አካል ጉዳተኞች የሚሠሩ ሥራዎች እንደ ዜጋ ሙብት መቆጠር አለበት፡፡» ስለዚህም የነገዋን ኢትዮጵያ ከማቆየት አንጻር ልጆች ላይ መሥራት እንዳለበት ያስረዳል፡፡

ሞገስ በያዝነው ዓመት የ‹ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች› ተከታዩን ክፍል ለማሳተም ቀን ቆርጦለታል። «ቀጣዩንም መጽሐፍ በብሬል የማሳተሙ ነገር ሳይታለም የተፈታ ነው» ይላል፡፡

በተያያዘም፤ «ወላጆች ልጆቻቸውን፣ ምግብ በማብላት፣ በማልበስ፣ ትምህርት ቤት በማስገባት ኃላፊነታቸውን የተወጡ አድርገው ያስባሉ፡፡ ከዚህ ይልቅ ለልጆቻቸው ጊዜ በመስጠት በመቀራረብ እና የነገ ሕይወታቸው ላይ መሥራት ይገባል፡፡» ያለው ሞገስ፤ ‹ቤተ አእምሮ› የተሰኘ ማሕበራዊ ትስስር ገጽ በመክፈት ወላጆች ለልጆቻቸው ማስነበብ ስላለባቸው መጽሐፍት እና ሌሎች መረጃዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ዩናይትድ ስቴትስ ሦስት የአፍሪካ አገራትን ከአጎዋ ማዕቀፍ ልትሰርዝ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚደንት ጆ ባይደን ኡጋንዳ፣ ጋቦን፣ ኒጀር እና ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክን ከአጎዋ ስምምነት ሊሰርዙ እንዳቀዱ ይፋ አደረጉ።

ፕሬዚደንቱ እንደገለጡት አገራቱ አንድ “ጅምላ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፈፅመዋል” አሊያም ዴሞክራሲያዊ ዕድገታቸው የዘገመ ነው።

አፍሪካ ግሮውዝ ኤንድ ኦፖርቹኒቲ አክት የተሰኘ መጠሪያ ያለው አጎዋ፤ በአውሮፓውያኑ 2000 ነው የተቋቋመው።

በዚህ ማዕቀፍ መሠረት ፈቃድ የተሰጣቸው ከሰሃራ በታች ያሉ አገራት ከ1800 በላይ ምርቶችን ከቀረጥ ነፃ ወደ አሜሪካ መላክ ይችላሉ።

ፕሬዚደንት ባይደን በአሁኑ ወቅት በወታደራዊ አመራር እየተዳደሩ ያሉት ኒጀር እና ጋቦን ከአጎዋ ማዕቀፍ ሊሰረዙ የሚችሉት “ፖለቲካዊ ብዝሃነት እና የሕግ



የበላይነትን ማስከበር ባለመቻላቸው ነው።”

ጋቦን እና ኒጀር በያዝነው የአውሮፓውያኑ ዓመት በመፈንቅለ መንግሥት ሲታመሱ እንደነበር ይታወሳል።

ባይደን አክለው ኡጋንዳ ከአጎዋ ማዕቀፍ ልትሰረዝና ተጨማሪ ማዕቀብ እንዲጣልባት የታሰበው ሃገሪቱ አከራካሪውን ፀረ-ተመሳሳይ ፆታ ሕግ በማውጣቷ ነው።

የተመሳሳይ ፆታ ወሲብ ሲፈፅሙ የተያዙ ግለሰቦች እስከሞት ድረስ ሊቀጡ ይችላሉ የሚለው ሕግ ዓለም አቀፍ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር።

ፕሬዚደንት ባይደን ለአሜሪካ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በላኩት ደብዳቤ ነው ይህን ዕቅዳቸውን የገለጡት።

“ምንም እንኳ ዩናይትድስ ስቴትስ ከማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ጋቦን፣ ኒጀር፣ እና ኡጋንዳ ጋር ውይይት ብታደርግም ሃገራቱ የአጎዋን መተባበር የሚለውን ሐሳብ መጣሳቸው ዩኤስን አሳስቧታል” ብለዋል።

አራቱ የአፍሪካ አገራት እስካሁን ያሉት ነገር የለም። 20ኛው የአጎዋ ፎረም ከሚመጣው ሐሙስ ጀምሮ በደቡብ አፍሪካ ይካሄዳል።

አገራቱ ከአጎዋ ማዕቀፍ የሚሰረዙት ከሚቀጥለው የአውሮፓውያኑ ዓመት መባቻ ጀምሮ ሲሆን ምጣኔ ሃብታቸውን ሊጎዳቸው እንደሚችል ይታመናል።

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለፈው ሳምንት ባወጣው መግለጫ ለጋቦን የሚደረገው እርዳታ ከሞላ ጎደል መቋረጡን ገልጦ ሃገሪቱ የሽግግር መንግሥት ካቋቋመች ብቻ እርዳታ ሊቀጥል እንደሚችል አሳውቋል።

የአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንተኒ ብሊንከን ባለፈው ነሐሴ ኒጀር ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚችል ጠቁመዋል።

ዩኤስ “የኒጀር መንግሥትን ሊጠቅሙ የሚችሉ የውጭ እርዳታዎችን ገታ ለማድረግ አስባለች” ብለው ነበር።

ቡርኪና ፋሶ፣ ማሊ እና ጊኒ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ከተካሄደባቸው በኋላ ከዚህ ቀደም ከአጎዋ ማዕቀፍ የተሰረዙ ሃገራት ናቸው።

## የታገቱትን የሉዊስ ዲያዝ አባት ለማግኘት ፖሊስ ፍለጋውን በተራራማ ቦታዎች አደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኮሎምቢያ ፖሊስ የታገቱትን የሊቨርፑሉን ኮከብ ተጫዋች አባት ለማግኘት ፍለጋውን በአገሪቱ ተራራማ ቦታዎች ማድረጉ ተሰማ።

ከጥቂት ቀናት በፊት የሊቨርፑል የክንፍ መስመር ተጫዋች ሉዊስ ዲያዝ ወላጆች በታጣቂዎች የመታገታቸው ዜና መሰማቱ ይታወሳል።

የአገሪቱ ጦር ከፖሊስ ጋር ተጣምሮ በሰሜናዊ ኮሎምቢያ ባደረገው ክትትል የተጫዋቹን እናት እሁድ ዕለት አግኝቶ ነበር።

የአገሪቱ ጦር የተጫዋቹን ወላጅ አባት ለማግኘት 120 ወታደሮችን በማሰማራት የመንገድ ላይ ፍተሻዎችን እያደረገ መሆኑን፣ ሄሊኮብተር ጨምሮ በሰው አልባ አውሮፕላን ፍለጋ እያደረገ መሆኑን አስታውቋል።

የአገሪቱ መንግሥት የሉዊስ ዲያዝን አባት ለማግኘት የሚያስችል መረጃ ለሰጠ 40ሺህ ፓውንድ ወሮታ እከፍላለሁ ብሏል።

ምንም እንኳ የኮሎምቢያ መንግሥት የተጫዋቹ እናት እና አባት በምን ሁኔታ እንደታገቱ ያለው ነገር ባይኖርም የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን ሉዊስ ማኔኤል ዲያዝ እና ሲሌኒስ ማሩላንዳ የተባሉት ወላጆቹ ነዳጅ ማደያ አቅራቢያ ሞተር ሳይክል ላይ በነበሩ የታጠቁ ሰዎች ታፍነው መወሰዳቸውን ዘግበዋል።

የተጫዋቹ ወላጆች የመታገታቸው ዜና እንደተሰማ ክለቡ ሊቨርፑል እና የቡድን አባላት ለዲያዝ ድጋፋቸውን እንደሚሰጡ ሲገልጹ ቆይተዋል።

ፊፋም እንዲሁ በፕሬዚዳንቱ ጊያኒ ኢንፋንቲኖ በኩል “በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ለተጫዋቹ እና ለቤተሰቡ ድጋፋችንን እንገልጻለን” ብሏል።

የኮሎምቢያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም የተጫዋቹ አባት ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ይለቀቁ ሲል ባወጣው መግለጫ ጠይቋል።

ከትናንት በስቲያ እሁድ ሊቨርፑል ከኖቲንግሃም ፎረስት በነበረው ጨዋታ ዲያዝ ሳይጫወት ቀርቷል።

የክለቡ ምክትል አሰልጣኝ ትናንት ምሽት ከጨዋታ በፊት በነበረ መግለጫ ላይ ዲያዝን “በጸሎታችን እያሰብነው ነው” ብለዋል። ምክትል አሰልጣኝ ፔፒጀን ሊጀናደርስ “በተቻለን መጠን ልንደግፈው ይገባል፤ አብዛኛዎቹ ነገሮች ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ናቸው” ብለዋል።

“ጸጥታ አስከባሪዎች አባቱን ያገኟቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፤ ያ እንዲሆን ጸሎታችን ነው” ብለዋል።

የኮሎምቢያ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ፍራንሲስ ባርቦሳ ምርመራውን በተመለከተ ለዲያዝ ማብራሪያዎችን እየሰጡት መሆኑን ገልጸው፤ ምናልባት ወላጅ አባቱ ወደ



ቬንዙዌላ ሳይሻገሩ እንደማይቀር ለተጫዋቹ ነግሬዋለሁ ብለዋል።

# ስፖርት




## የጁዶ ስፖርትን በአጭር ጊዜ ውጤታማ የማድረግ ጅምር

ዓለማየሁ ግዛው

የዘመናዊ ስፖርት መሠረቶች ባህላዊ ጨዋታዎችና እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ከሚዘወተሩ የባህል ስፖርቶች መካከል አንዱ ትግል ሲሆን ከኦሊምፒክ ውድድሮች መካከል አንዱ ከሆነው የጁዶ ስፖርት ጋር ተቀራራቢ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተዘውታሪ የሆነውን ባህላዊ ስፖርት ከዘመናዊው ጋር በማቀናጀት ውጤታማ መሆን ቢቻልም ብዙ አልተሠራበትም፡፡ በቅርቡ በብሔራዊ ደረጃ ዕውቅና አግኝቶ በፌዴሬሽን ደረጃ የተመሠረተው የጁዶ ስፖርት፤ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ከምትሳተፍባቸው ስፖርቶች መካከል አንዱ ለመሆን አቅዶ እንቅስቃሴውን ጀምሯል፡፡

በኢትዮጵያ ካሉ የስፖርት ማኅበራት 32ኛው ሆኖ የተመዘገበው ጁዶ ለዓመታት የዘለቀ እንቅስቃሴ ቢኖረውም ተዘውታሪነቱ ግን የተገደበ ነበር፡፡ ላለፉት ዓመታት የጎላ እንቅስቃሴ የነበረውም በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ኦሮሚያ ክልሎች ሲሆን፤ ሀገር አቀፍ ደረጃ እንደ ፌዴሬሽን ዕውቅና ማግኘቱን ተከትሎም የተሻለ እድገት ይኖረዋል ተብሎ ተስፋ ተደርጎበታል፡፡ ፌዴሬሽኑ አዲስ እንደመሆኑ በቅደም ተከተል በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ቢጠበቅበትም፤ በጥቂት ክለቦች እና ግለሰቦች የተገደበውን ስፖርት በተደራጀና ወጥ በሆነ አካሄድ ተዘውታሪነቱን ለማስፋት እንደሚሠራ ጠቁሟል፡፡ ከተወዳዳሪነትና ውጤታማነት ጋር በተያያዘም ስፖርቱ ባህላዊ መሠረት ያለው በመሆኑ በአጭር ጊዜ የተሻለ ደረጃ ላይ የመድረስ ዕድል እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡



የኢትዮጵያ ጁዶ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ማስተር ወንድሙ ደሳለኝ፤

የጁዶ ስፖርት ከትግል ስፖርት ጋር ያለው ተቀራራቢነት ፌዴሬሽኑ እምቅ አቅም ያላቸውን ስፖርተኞች በስፋት ለማግኘት ያስችለዋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡ የባህል ስፖርተኞች የተሻሉ ታጋዮች በመሆናቸው ከዘመናዊው የጁዶ ስፖርት ጋር በማቀናጀት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥሩ ተፎካካሪና ተወዳዳሪ ስፖርተኞችን ለማፍራት ጥረት የማድረግም እቅድም በፌዴሬሽኑ በኩል ተወጥኗል፡፡ በትልቁ ዓለም አቀፍ የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ ላይ ኢትዮጵያ የምትወከልበት ስፖርት እንዲሆን ለማስቻልም ጥረት እንደሚደረግ ተጠቁሟል፡፡

የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ማስተር ወንድሙ ደሳለኝ እንደሚናገሩት፣ ጁዶ ከኦሊምፒክ ስፖርቶች አንደኛው እንደመሆኑ በብሔራዊ ደረጃ በፌዴሬሽንነት ተመዝግቦ እንቅስቃሴ አለማድረጉ የዘገየና ስፖርቱ እንዳያድግ ያደረገ ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ ስፖርቱ በሚገባው ልክ ማደግ ባለመቻሉ ኢትዮጵያ በበርካታ ኦሊምፒኮች በጁዶ ሳትሳተፍ መቅረቷም የሚያስቆጭ መሆኑንም ፕሬዚዳንቱ ይገልጻሉ፡፡ አሁን በብሔራዊ ደረጃ እውቅና ማግኘቱም ለስፖርቱ በርካታ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ሲሆን፤ የመጀመሪያውና ዋነኛው ስፖርቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋና እንደልብ ለመንቀሳቀስም የሚያግዝ ነው፡፡ በኦሊምፒክ ኢትዮጵያን መወከል የሚችሉ ስፖርተኞችን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማፍራት የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራትም መንገድ ይከፍታል፡፡ ስፖርቱ በስፋት ሲዘወተርና ሲስፋፋ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ሀገራቸውን የሚወክሉ ስፖርተኞችን እንዲወጡ የሚረዳም ይሆናል፡፡

ከተጠቀሱት ነጥቦች ባሻገር ጁዶ በፌዴሬሽን ደረጃ መቋቋሙ የሚያስገኘው ጥቅም በጣም ብዙ መሆኑን የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፤ የጁዶ ስፖርት እንደሌሎች የፍልሚያ ስፖርቶች በቀላሉ የሚሠራ አለመሆኑን ያብራራሉ፡፡ ሌሎች የፍልሚያ ስፖርቶች እንደልብ በአደራሾች ውስጥ በቀላሉ የሚከወኑ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ጁዶ የመወርወርና የመጣል ዓይነት ባህሪን በመላበሱ ለስፖርቱ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ያስፈልጉታል። እነዚህን ቁሳቁሶች ለማሟላትና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ ለማግኘት ሀገር አቀፍ ዕውቅናው የሚያግዘው ይሆናል፡፡ ለስፖርቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ የማይገኙ በመሆኑ ለማሟላት ሰፊ ጊዜ ያስፈልጋል፡፡ የራሱ የሆነ ልብስና ምንጣፍ የሚያስፈልገው ሲሆን ውድና በቀላሉ የማይገኙም ናቸው፡፡ ስለዚህም ከኤምባሲዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ጥቅም ላይ የዋሉትን በእርዳታ መልኩ ለማሰባሰብና ግዢዎችን አድርጎ ለማቅረብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ፌዴሬሽን መሠረቱ ከአስፈላጊም በላይ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ አሠራርን በመከተል ለስፖርቱ የሚያስፈልገውን መሣሪያ በእርዳታና በግዢ ማምጣት ያስችለዋል፡፡

ፌዴሬሽኑ በቅደም ተከተል መሠራት የሚገባቸውን ሥራዎችን ካከናወነ በኋላም ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመተባበር ስፖርተኞችን በአንድ በማሰባሰብ ወደ ሥልጠና እንደሚገባም አስታውቋል፡፡ ወደ ውድድር ከመግባቱ በፊት አንድ ማዕከል ውስጥ በመሰበሰብ ብቁ የሆኑ ሰልጣኞች፣ አሰልጣኞችና ዳኞች ማሰልጠን የመጀመሪያ ሥራው ይሆናል፡፡ ይህንንም ለመከወን እቅዱን መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውም ታውቋል፡፡

ስፖርቱ አዲስ በመሆኑና እንደ ሌሎቹ በስፋት ባለመታወቁ ከመንግሥት ጀምሮ አስፈላጊው ድጋፍ ከሚመለከታቸው አካላት እንዲደረግለት ጥሪ አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም ስፖርቱ የኦሊምፒክ ስፖርት እንደመሆኑም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴም ድጋፉን እንዲያደርግና ስፖርቱን በጋራ በመደገፍ በአጭር ጊዜ ውጤታማ ማድረግ ይገባል፡፡ ስፖርቱን ለማሳደግ እቅዶችን በመንደፍና ባለሀብቶችን በማሳተፍ የፋይናንስ ምንጩን ለማስፋት የሚሠራም ይሆናል፡፡


# የጨረታ ማስታወቂያ

## የጨረታ ቁጥር አ/አ/ኢ/ኮ 01/2016

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የግዢ ንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ለስራ ክፍሎች አገልግሎት የሚውሉ

ሎት 1. አላቂ የፅህፈት እቃዎችና ልዩልዩ መሳሪያዎች ሎት 5. የፈርኒቸር እቃዎች

ሎት 2. የፅዳት እቃዎች ሎት 6 የህትመት ውጤቶች

ሎት 3. የኤሌክትሮኒክ እቃዎች ሎት.7 የመኪና ጌጣጌጥ

ሎት 4. የሰራተኛ ደንብ ልብስ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በጨረታ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡

1. አግባብነት ያለው የታደሰ ንግድ ፈቃድ እና የዘመኑን ግብር የከፈለ እንዲሁም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም በአ/አ/ከ/አ/ፋይናንስ ቢሮ በእቃ አቅራቢነት ዝርዝር ለመመዝገባቸው ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያላቸው እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፣ ታክስ ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር ሎት1.ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/፣ ለሎት 2. ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/፣ ለሎት 3.ብር 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/፣ ለሎት 4 ብር 10,000.00/አስር ሺህ ብር/ ለሎት 5. ብር 5,000.00/አምስት ሺህ ብር/፣ ለሎት 6. ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/፣ ለሎት 7 የመኪና ጌጣጌጥ ብር 5,000.00/አምስት ሺህ/ ብቻ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ(CPO) ብቻ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር ለእያንዳንዱ ሎት ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር / በመክፈል ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በፋይናንስ ዳይሬክቶሬት /ሠንጋ ተራ /ዮቢክ ኮሜርሻል ሴንተር 8ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 801A በመቅረብ መውሰድ ይቻላል፡፡
5. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተከታታይ 10/አስር/ የስራ ቀናት በአየር ላይ ከዋለ በኋላ በ11ኛው/ በአስራ አንደኛው /ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ተዘግቶ በዚሁ ቀን የስራ ቀን ከጠዋት 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በግዥ ንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት 8ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 802 ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዳቸውን በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሰረት ሞልተው ማህተም በማድረግ ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች ዶክመንታቸውን ዋናውንና ኮፒውን ለየብቻ በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዋጋ በተነገራቸው ቀን ቀርበው ውላቸውን በመፈፀም ውል ማስከበሪያ 10% በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
9. ተጫራቾች በሚያቀርቡት ዋጋ ላይ ቫትን አካተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ተጫራቾች የሚጫረቱባቸውን እቃዎች ለመለየት የሚያስችል ናሙና ማቅረብ ወይም ስፔስፊኬሽን ወይም በፎቶ የተደገፈ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
11. አንድ ተጫራች ሌላው ከሰጠው ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡
12. አሸናፊው ድርጅት ውል ከፈረመበት በ15 ቀን ውስጥ እቃውን ያቀርባል፡፡
13. ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለወጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግ ወይም ከጨረታው እራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡
14. ተጫራቾች የተጠቀሱትን እቃዎች በሙሉ ወይም በከፊል መጫረት ይችላሉ ፡፡
15. መስሪያ ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ ማብራሪያ** - ከፈለጉ ከግዥ ንብረት አስተዳደር ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት 8ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 802 በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 011557-78-46/ ደውለው ያነጋግሩ

**አድራሻ፡-** ልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 09 ዩቢክ ኮሜርሻል ሴንተር

**በአዲስ አበባ ከ/አስ/ር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የግዥ ንብረት አስተዳደር እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት**